# ስለ ስቅለት እስላማዊ ብዥታዎች

## ለያሕያ ኢብኑ ኑህ 42 የኩረጃ ጥያቄዎች የተሰጠ ምላሽ

[www.ewnetlehulu.org](www.ewnetlehulu.org)

የመጽሐፉ ርዕስ፡- የስቅለት ብዥታዎች

ንዑስ ርዕስ፡- ስቅለትን አስመልክቶ መመለስ ያለባቸው 42 መሠረታዊ ጥያቄዎች

ደራሲ፡- ያሕያ ኢብኑ ኑህ

የገፅ ብዛት፡- 29

የሕትመት ዘመን፡- 2011

አሳታሚ፡- አልተገለጸም

*“የትጉህ አሳብ ወደ ጥጋብ ያደርሳል፤ ችኩል ሰው ሁሉ ግን ለመጕደል ይቸኩላል።" (ምሳሌ 21፡5)*

*“የታመነ ሰው እጅግ ይባረካል፤ ባለጠጋ ለመሆን የሚቸኵል ግን ሳይቀጣ አይቀርም።” (ምሳሌ 28፡20)*

በዚህ ሰሞን እየታተሙ በመውጣት ላይ የሚገኙት እስላማዊ መጻሕፍት በእጅጉ አስገራሚ ናቸው፡፡ ይዘታቸው ገለባ ከመሆኑም ባለፈ የሸከፏቸው የተዛቡ መረጃዎችና የተሰረቁ ሐሳቦች ብዛት የማይታመን ነው፡፡ ይህም እነዚህ ወገኖች በእጃቸው ላይ የሚገኘውን ኮተት ሁሉ አሳትመው ገንዘብ ለማግበስበስ ያላቸውን ጥድፍያ የሚያመለክት ሲሆን በዚህ ጥድፊያ ወቅት በሚያስተላልፉት ያልተጣራ መረጃ ምክንያት በየዋሁ ሕዝብ ላይ የሚደርሰው ጉዳት ግድ አይሰጣቸውም፡፡ ከክርስቲያን ዐቃቤ እምነታውያን የብረት ጋሻ ጋር ተላትመው መሰባበራቸውንም ከስሌት ውስጥ አያስገቡም፡፡ ይህ አካሄዳቸው ትክክል አለመሆኑንና ከማሕበራዊ ሚድያ መድረክ አልፈው የሕትመቱን ዓለም ለመቀላቀል የሚያበቃ ዕውቀትም ሆነ ብስለት እንደሌላቸው በመግለፅ ከቅንነት የመነጨ ምክር ብንለግሣቸውም ሊሰሙን አልወደዱም፡፡ ይባስ ብለው ምክራችንን ከስጋት የመነጨ እንደሆ በማስመሰልና ለሙግቶቻቸው “ጥንካሬ” እንደ ማረጋገጫ በመቁጠር አሻፈረኝ ብለዋል፡፡ እኛም የነዚህን ወገኖች የተጭበረበረ አካሄድና የሙግቶቻቸውን ደካማነት ሰልማን ኮከብ ለተሰኘው ደራሲ በሰጠነው ምላሽ ጀምረናል፡፡ (ምላሹን ለማንበብ **[እዚህ ጋ]()** ይንኩ)፡፡ እነሆ አሁን ደግሞ ተራው የያሕያ ኢብኑ ኑህ ነው፡፡ ይኸኛውም ወገናችን እንደ ሰልማን ሁሉ ለመልስ የሚመጥን ጽሑፍ ባያዘጋጅም ዳሩ ግን አንዳንድ ሙስሊም ወገኖቻችን ስሁት ሙግቶቹን በመያዝ እየሳቱ ስለሚገኙ መልስ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ ታይቶናል፡፡

ደራሲው በመክፈቻው ላይ እንዲህ ይለናል፡-

> **መክፈቻ**
>
> የኢየሱስ ስቅለትን አስመልክቶ ያዘጋጀኋት ይህች አነስተኛ መጽሀፍ በተለያዩ ጊዜያት ክርስትናን ሳጠና ይፈጠሩብኝ የነበሩ ጥያቄዎችን መሰረት አድርጌ ነው። መጽሀፉ እንደ ሙስሊም የኔን ኢስላማዊ አመለካከት የሚገልጽ ሳይሆን መሰረቱ ፍጹም መጽሀፍ ቅዱስ ላይ ብቻ ሁኖ ክርስቲያኖች ስቅለትን ሲያምኑ ልብ ሊሏቸው የሚገቡ መሰረታዊ ጥያቄዎችን የሚያስገነዝብ ነው።

ይህ ሰው ክርስትናን ሲያጠና ከተፈጠሩበት ጥያቄዎች በመነሳት እነዚህን ጥያቄዎች አንዳቀረበ ቢገልፅም ጥያቄዎቹን በሙሉ አንዲት ቃል እንኳ ሳይጨምርና ሳይቀንስ በሌላ ሰው ከተጻፈ ጽሑፍ ላይ ነው የገለበጠው፡፡ ይህ ሰው በምንጭነት የተጠቀመው “65 Reasons to Believe Jesus Did Not Die on the Cross” በሚል ርዕስ አይ. ኤች. ከውሰር በተሰኘ አውስትራሊያዊ የአሕመዲያ ኢማም የተጻፈውን ጽሑፍ ሲሆን ሙሉ ጽሑፉ ድረገፅ ላይ ሰፍሮ ይገኛል፡፡ ዐይቶ ማረጋገጥ ለሚፈልግ አንባቢ የድረገፁ አስፈንጣሪ እነሆ፡- https://themuslimtimes.info/2012/04/14/65-reasons-to-believe-jesus-did-not-die-on-the-cross/

የራሱን ሐሳብ ሳያክል የሌላ ሰው *ሥራ* ቃል በቃል ቀድቶ ከተረጎመ በኋላ የትርጉም *ሥራ* መሆኑን ለአንባቢያኑ እንደመግለፅ በግል ጥናቱ ያገኘው መሆኑን መናገሩ ትልቅ ቅሌት ነው፡፡ እንዲህ ያለ አስነዋሪ ተግባር አንባቢን መናቅ ነው፡፡ እንኳንስ ከአንድ መንፈሳዊ መጽሐፍ ከሚጽፍ ሰው ይቅርና ከዓለማውያን ጸሐፍት እንኳ የማይጠበቅ ጸያፍ ድርጊት ነው፤ በቅጂ መብት ጥሰት የሚያስጠይቅ ወንጀልም ነው፡፡ ዳሩ ግን መቅዳት የነቢዩ ሱና በመሆኑ ይህ የሐሳብ ስርቆት ለደራሲው ቀላል መስሎ ሊታየው ይችላል፡፡ የእስልምና ዋና መመርያ የሆነው ቁርአንስ ቢሆን ከመጽሐፍ ቅዱስ፣ ከአይሁድ ታልሙድ፣ ከአፖክሪፋ፣ ከአረብ ፓጋኖች፣ ከዞራስትሪያኒዝምና ከመሳሰሉት ምንጮች የተቀዳም አይደል?

መሐመድ በዙርያው ከነበሩት ባሕሎች ሐሳቦችን ይወስድ እንደነበር በእስላማዊ ምንጮች የተረጋገጠ በመሆኑ ይህንን እውነታ ማስተባበል አይቻልም፡-

> ኢብን አባስ እንዳወራው ነቢዩ ከአላህ ዘንድ ትዕዛዝ በሌለባቸው ጉዳዮች ላይ የመጽሐፉን ሰዎች (አይሁድና ክርስቲያኖች) የሚያደርጉትን ቀድቶ ያደርግ ነበር… (ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅፅ 7፣ መጽሐፍ 72፣ ቁጥር 799)

> አል-በራ እንዳወራው ለአስራ ስድስት ወይንም አስራ ሰባት ዓመታት ያህል ወደ ኢየሩሳሌም ዞረን እንሰግድ ነበር፡፡ ከዚያም አላህ ፊቱን ወደ ቂብላ (መካ) እንዲያዞር ነገረው፡፡ (ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅፅ 6፣ መጽሐፍ 60፣ ቁጥር 19)

> አነስ እንዳወራው እስልምናን የተቀበለ አንድ ክርስቲያን ነበረ፤ ይህ ሰው ምዕራፍ 2 እና 3ን ያነብ የነበረ ሲሆን ለነቢዩ (ቁርአንን) ጸሐፊ በመሆን ያገለግል ነበር፡፡ ኋላ ላይም ወደ ክርስትናው በመመለስ እንዲህ ሲል አወራ፡- “መሐመድ እኔ ከጻፍኩለት ነገር ውጪ ምንም ነገር አያውቅም፡፡” ከዚያም አላህ ገደለው… (ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅፅ 4፣ መጽሐፍ 56፣ ቁጥር 814)

የኩረጃ ሃይማኖት የሚከተል ሰው ከሌላ ምንጭ ቃል በቃል የኮረጀውን በራሱ ጥናት የደረሰበት በማስመሰል ቢያቀርብ አያስገርምም፡፡

ሌላው እብለት መጽሐፉ እስላማዊ አመለካከቱን እንደማያንፀባርቅ መግለፁ ነው፡፡ በስቅለት ታሪካዊነት ዙርያ ብዥታ ያለባቸው ብቸኛ ሕዝቦች ሙስሊሞች በመሆናቸው መጽሐፉ እስላማዊ አመለካከቱን እንደማያንጸባርቅ መናገሩ አስገራሚ ነው፡፡ የግለሰቡ የሙግት መነሻም ሆነ መድረሻ በስቅለት ዙርያ የሚገኘው እስላማዊ ብዥታ ነው፡፡ የክርስቶስ ስቅለት ታሪካዊነት ከመጀመርያው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በነበሩት ሮማውያን፣ አይሁድ፣ ግሪክና ክርስቲያን የታሪክ ጸሐፍት የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ በቅዱሳት ነቢያት አስቀድሞ የተተነበየና በሐዋርያት ምስክርነት የጸና ነው፡፡ ነገር ግን እስልምና ስለ ስቅለት ያለው እምነት ከክስተቱ ከስድስት ክፍለ ዘመናት በኋላና ከቦታው በአንድ ሺህ ኪሎሜትሮች ርቆ በኖረ በአንድ ሰው በተነገረ አንድ አሻሚ ጥቅስ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ደራሲው እንዲህ ይላል፡-

> “እስልምና የኢየሱስን ስቅለት አስመልክቶ ግልጽ አስተምህሮ ስላለው ከነዚህ ጥያቄዎች ሁሉ የራቀ ነው፡፡”

በነገራችን ላይ የክርስቶስ ስቅለት የታሪክ ሃቀኝነት ጉዳይ እንጂ የሃይማኖታዊ አስተምሕሮ ጉዳይ አይደለም፡፡ በስቅለቱ ነገረ መለኮታዊ ምልከታ ዙርያ መከራከር ይቻላል፤ ነገር ግን ክርስቶስ አልተሰቀለም የሚል ሃይማኖታዊ አስተምሕሮ ፈጥሮ መከራከር ከታሪክ ሃቅ ጋር መላተም ነው፡፡ በምሑራን ዘንድ ክብደት የሚሰጣቸው የታሪክ መዛግብት በሙሉ ክርስቶስ እንደተሰቀለ ይናገራሉ፡፡ ለምሳሌ ያህል፡-

- ታሉስ (55 ዓ.ም.)
- ማራ በር ሴራፒዮን (70 ዓ.ም.)
- ታሲተስ (64 ዓ.ም.)
- ፕሊኒ (110 ዓ.ም.)
- የሰሞሳታው ሉሺያን (115-200 ዓ.ም.)
- ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን (90 ዓ.ም.)
- የባቢሎናውያን ታልሙድ (> 200 ዓ.ም.)
- ሱቶኒየስ (49 ዓ.ም.)

በዚህ ዘመን የክርስቶስን ስቅለት የሚክድ የታሪክ ሊቅ በዓለም ላይ ፈልጎ ማግኘት አዳጋች ነው፡፡ ማንም ነቢይ ነኝ ባይ ወደ ዋሻ ገብቶ በመውጣት መልአክ ታይቶኛል በሚል ቅዠት ይህንን ሃቅ መለወጥ አይችልም፡፡

ደራሲው እስልምና በስቅለት ዙርያ ያለውን እርግጠኛነት አጉል በተወጠረ የራስ መተማመን ከገለጸ በኋላ አለኝ ያላትን ብቸኛዋን አሻሚ እስላማዊ ማስረጃ ከቁርአን ይጠቅሳል፡-

> “እኛ የአላህን መልክተኛ የመሬምን ልጅ አልመሲሕ ዒሳን ገደልን በማለታቸው (ረገምናቸው)፤ አልገደሉትም፤ አልሰቀሉትምም ግን ለነሱ (የተገደለው ሰው በዒሳ) ተመሰለ እነዚያም በርሱ ነገር የተለያዩት፣ ከርሱ (መገደል) በመጠራጠር ውስጥ ናቸው፤ ጥርጣሬን ከመከተል በስተቀር በርሱ ነገር ምንም ዕውቀት የላቸውም፤ በእርግጥም አልገደሉትም።” (ቁርአን 4፡157)

ይህችን ነጠላ “ማስረጃ” ይዞ ነው እንግዲህ “እስልምና የኢየሱስን ስቅለት አስመልክቶ ግልጽ አስተምህሮ ስላለው ከነዚህ ጥያቄዎች ሁሉ የራቀ ነው” የሚል ሰበካ የሚያቀርብልን፡፡ ሲጀመር ጥቅሱ የኢየሱስን አለመሰቀል ይገልፃል ከተባለ ከታሪካዊ ማስረጃዎች ጋር ስለሚጋጭ ውሸት ነው፡፡ እንዲያም ሆኖ ብዙ የሐሳብ ግድፈቶችና አመክንዮአዊ ችግሮች አሉበት፡-

1. ይህ ጥቅስ በአረብኛው ግልፅ ካለመሆኑ የተነሳ ተርጓሚዎች በአረብኛ ቁርአን ንባብ ውስጥ የሌሉ ቃላትን በመጨመር ትርጉም እንዲሰጥ ለማድረግ ሞክረዋል፡፡ በቅንፍ የተጨመሩት በሙሉ በአረብኛው ቁርአን ውስጥ የሉም፡፡ ብዥታ ባይኖርበት ኖሮ የሰው ቃልና ማብራርያ ማከል ባላስፈለገ ነበር፡፡
2. ጥቅሱ አይሁድ ዒሳን አንዳልገደሉት እንጂ ዒሳ እንዳልተገደለ አይናገርም፡፡ ሙስሊሞች “ዒሳ አልሞተም” የሚል አንድ ጥቅስ ከቁርአን ውስጥ ማሳየት አይችሉም፡፡
3. ይህ ጥቅስ ለተለያዩ ትርጓሜዎች ከተጋለጡት የቁርአን ጥቅሶች መካከል አንዱ ነው፡፡ ለዚህ ነው የአሕመዲያና የኔሽን ኦፍ ኢስላም ቡድኖች ዒሳ እንደተሰቀለ የሚያምኑት፡፡ ይህ ጥቅስ አሕመድ ዲዳትና ሻቢር አሊን የመሳሰሉት ሙስሊም ዐቃቤ እምነታውያን የዒሳን መሰቀል እንዳያምኑ አላገዳቸውም፡፡ ሙስሊም ሰባኪያን እስልምና በሁሉም ረገድ ፍፁም አንድ እንደሆነ በማስመሰል የሚናገሯት ነገር አስቂኝ ናት፡፡
4. ከዚህ ጥቅስ በመነሳት በዒሳ ምትክ የሆነ ሰው እንደተሰቀለ የሚያምኑት ሙስሊሞች በተሰቃዩ ማንነት ዙርያ ስምምነት የላቸውም፡፡ አንዳንዶች ከአይሁድ መካከል አንዱ ተሰቅሏል በማለት ሲናገሩ ሌሎች ደግሞ የተሰቀለው ከሮማውያን ወታደሮች መካከል አንዱ ነው ይላሉ፡፡ ከዒሳ ተከታዮች መካከል አንዱ በፍቃደኝነት መሞት ስለፈለገ አላህ የዒሳን መልክ ሰጥቶት ተሰቀለ የሚሉም አሉ፡፡ “የበርናባስ ወንጌል” በሚል ስም በመካከለኛው ዘመን በአንድ ሙስሊም የተጻፈ መጽሐፍ ደግሞ በምትኩ የሞተው የአስቆሮቱ ይሁዳ ነው ይላል፡፡ ነገር ግን ለነዚህ ሁሉ እስላማዊ መላምቶች ድጋፍ የሚሰጥ አንድ ጥቅስ እንኳ በቁርአን ውስጥ አይገኝም፡፡ ቁርአን እንኳንስ በምትኩ ሞተ የተባለውን ሰው ስም ሊጠቅስ ይቅርና ሌላ ሰው ስለመሞቱ እንኳ ፍንጭ አይሰጥም፡፡ ሙስሊም ተርጓሚዎች ናቸው በቅንፍ ቃላትን እየጨመሩ የሚያወናብዱት፡፡
5. በዒሳ ምትክ ሌላ ሰው ተሰቅሏል የሚለው ግምት ፈጣሪን የማጭበርበር ተዋናይ የሚያስመስል ትርክት ሲሆን ዒሳ የተሰቀለ በማስመሰል ከክስተቱ በኋላ የሚገኙትን ሰዎች ስላታለለ በዚህ ምክንያት ለተፈጠረው “ስህተትና ጥፋት” ሁሉ ፈጣሪን ተጠያቂ የሚያደርግ ደካማ ትርክት ነው፡፡
6. ጥቅሱ ሌላም ታሪካዊ ስህተትም አለበት፡፡ በጥቅሱ መሠረት አይሁዶች ኢየሱስን የአላህ መልእክተኛና አልመሲህ (ክርስቶስ) ብለው ጠርተውታል፡፡ ነገር ግን ክርስትናን ላልተቀበለ አይሁዳዊ የናዝሬቱ ኢየሱስን “የአምላክ መልእክተኛና መሲህ” ብሎ መጥራት ታላቅ ክህደት ነው፡፡

ይህ ጥቅስ የሚያስከትላቸውን ሌሎች አያሌ ችግሮች ለመረዳት እስልምናና የመሲሁ ስቅለት በሚል ርዕስ የተጻፈውን ጽሑፍ ይመልከቱ፡፡

# የብዥታ ጥያቄዎች

ደራሲው እስላማዊ ብዥታውን ወደ ክርስቲያኖች ለማስተላለፍ የተለያዩ ጥያቄዎችን ያነሳል፡፡ አንድ በአንድ እንደሚከተለው እናያቸዋለን፡፡

1. <u>ስቅለት ለምን?</u>

አይሁዳውያን እየሱስን ሊሰቅሉት የፈለጉበት ዋነኛ አላማ እርሱ የሚወደድ የአምላክ ልጅ እንዳልሆነና የአምላክ እርግማን በርሱ ላይ እንደነበር በወቅቱ ለነበረው ህዝብ ለማሳየት ነበር። አይሁዳውያን ከብዛት አንፃር በሙቶ ሺዎች የሚቆጠሩ እንደመሆናቸው መጠን እየሱስን በቀላሉ ለመግደል የሚያዳግታቸው ምንም ነገር አልነበረም። አላማቸው እንዲሁ ዝምብሎ እሱን መግደል ቢሆን ኖሮ ልክ ሰላሳ ዲናር ከፍለው እንዳገኙት ሁሉ በተመሳሳይ መንገድ ከፍለው ማስገደል ይችሉ ነበር። ነገር ግን ዋነኛ አላማቸው በአደባባይ አዋርዶ በፍርድ በማስገደል ለሌላው ህዝብ ከአምላክ ያልተላከ ሀሡተኛ መሲህ እንደሆነ ማሳየት ነበር። በርግጥም ከአምላክ ዘንድ ከሆነ ያለምንም ጥርጥር አምላክ ያድነዋል ካልሆነ ግን ልክ እንደማንኛውም ወንጀለኛ ነው የሚለውን ህዝቡ ይረዳ ዘንድ ይፈልጉ ነበር። ይህ በአይሁዶች ዘንድ የነበረው አመለካከት ነበር። በዚህ ረገድ ላስተዋለ ሰው እየሱስ መሰቀሉ የነሱን አላማ ያሳካዋል እንጅ የተለየ ትርጉምን አይሰጠንም።

አንደኛ፡- ኢየሱስ መሞት በሚያስፈልገው ሰዓት ራሱን ለሞት አሳልፎ ሰጠ እንጂ አይሁድ ሊገድሉት ስለፈለጉ ብቻ አልሞተም፡፡ አይሁድ በቁጣ ተነሳስተው ሊገድሉት ብዙ ጊዜ ሞክረው አቅቷቸዋል (ሉቃስ 4፡28-30፣ ዮሐንስ 7፡30፣ 8፡20)፡፡

ሁለተኛ፡- ኢየሱስ በወቅቱ ብዙ ተከታዮችን አፍርቶ ስለነበር የአይሁድ መሪዎች ሊገድሉት ቢፈልጉም ሕዝቡን ግን ይፈሩ ስለነበር ምቹ እና አሳማኝ አጋጣሚን መጠበቅ ግድ ብሏቸው ነበር (ማርቆስ 11፡18፣ ሉቃስ 22፡2)፡፡

ሦስተኛ፡- የአይሁድ መሪዎች ኢየሱስ እውነተኛ መሲህ እንዳልሆነ ለማረጋገጥ መሞከራቸው እውነት ቢሆንም ኢየሱስን እንዲሰቀል ማድረጋቸው የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ፍፃሜ በመሆኑ በገዛ ምናባቸው መሲህ አለመሆኑን ቢያስቡም ክስተቱ ግን መሲህነቱን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ መሲሑ እንደሚንገላታ፣ እንደሚቸነከር፣ እንደሚወጋ፣ እንደሚሰደብ፣ እንደሚሞት፣ ልብሱን ወታደሮች እንደሚከፋፈሉ ወዘተ. በነቢያት ተነግሯል (መዝሙር 22፡12-18፣ ኢሳይያስ 53፣ ዘካርያስ 12፡10)፡፡ ይህ መለኮታዊ ትንቢት እስከተፈፀመ ድረስ አመፀኛ አይሁድ የፈለጉትን ቢያስቡ ግድ የሚለው ማን ነው?

አራተኛ፡- ኢየሱስ ሞትን ድል አድርጎ በመነሳት የአይሁድ መሪዎችን ጥረት አከሸፏል፤ እሳቤያቸውም ትክክል እንዳልሆነ አረጋግጧል፡፡

ስለዚህ የጠያቂው ሙግት ክብደት የሚሰጠው አይደለም፡፡

2. <u>ይሰቀል ዘንድ ማን ፈለገ?</u>

እየሱስ ይሰቀል ዘንድ ይፈልጉ የነበሩት እነማን ናቸው? የሚለውን አስመልክቶም መፅሀፍ ቅዱስ ወጥ የሆነ ትምህርት የለውም። በተለያዩ ቦታዎች የተለያዩ ሰዎችን በመጥቀስ በዚህ ዘርፍ ሊኖረው የሚገባውን ግልጽነት ነፍገውታል። ሉቃስ ለዚህ ተግባር የካህናት አለቆችንና መኳንንቶችን ተጠያቂ ያደርጋል።

*"፤ እርሱንም የካህናት አለቆችና መኳንንቶቻችን ለሞት ፍርድ አንዴት አሳልፈው እንደ ሰጡትና እንደ ሰቀሉት ነው።" (የሉቃስ ወንጌል 24:20)*

በሌላ ቦታ ላይ ደግሞ ይህንን ቅጣት ይፈልጉ የነበሩት ጥቂት ሰዎች ሳይሆኑ ህዝቡ ሁሉ እንደነበር ይነግረናል።

*ጲላጦስ፦ ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን እንግዲህ ምን ላድርገው? አላቸው፤ ሁሉም፦ ይሰቀል አሉ። ገዢውም፦ ምን ነው?ያደረገው ክፋት ምንድር ነው?አለ፤ እነርሱ ግን፦ ይሰቀል ኢያሉ ጩኸት አበዙ። ጲላጦስም ሁከት እንዲጀመር እንጂ አንዳች እንዳይረባ ባየ ጊዜ፥ ውኃ አንሥቶ፦ እኔ ከዚህ ጻድቅ ሰው ደም ንጹሕ ነኝ፤ እናንተ ተጠንቀቁ ሲል በሕዝቡ ፊት እጁን ታጠበ። ሕዝቡም ሁሉ መልሰው፦ ደሙ በእኛና በልጆቻችን ላይ ይሁን አሉ። (የማቴዎስ ወንጌል 27:22-25 )*

**ታዲያ እየሱስ ይሰቀል ዘንድ የፈለጉት እነማን ናቸው? ጥቂቱ ማህበረሰብ ወይንስ መላው ህዝብ? ይህም በስቅለት ታሪክ ውስጥ ካሉ ያልጠሩ ብዥታዎች መካከል አንዱ ነው።**

*መሪዎች የኢየሱስን መሞት ይፈልጉ ነበር፤ ሕዝቡም ሐሳባቸውን እንዲደግፍ አነሳሱት፡፡ ይህ ብዥታን ሊፈጥር የሚችለው እንዴት ነው? እንዲህ ያለ ገለባ ሙግት አይቼም አላውቅ!*

3. <u>ስቅለቱን የፈለጉት አይሁዳውያን ነበሩ</u>

የእየሱስ ስቅለት በዋነኝነት ትርጉም የሚሰጠውና ጠቃሚ የሆነው ለክርስቲያኖች ነው። እንደ ክርስቲያኖች አመለካከት እየሱስ ለእነሱ ሀጥያት ብሎ በመስቀል ላይ በመሞት እዳቸውን ከፍሎላቸዋል። ነገር ግን የስቅለትን ዳራ ስንመለከተው ግን የስቅለቱ ታሪክ ወደዚህ የእምነት ሒደት አይመራንም። በአንድ ወቅት በአይሁዳውያንና በሱ መካከል በነበረ አለመግባባት አይሁዳውያን እንዲሞት በመፈለጋቸው ምክንያት በገዥው ፊት አቅርበው እንዲፈረድበት አድርገዋል። በቃ ታሪኩ አበቃ።


*ጲላጦስም፦ እነሆ ሰውዬው አላቸው። የካህናት አለቆችና ሎሌዎች ባዩትም ጊዜ፦ ስቀለው ስቀለው ኢያሉ ጮኹ። ጲላጦስም፦ እኔስ አንዲት በደል ስንኳ አላገኘሁበትምና እናንተ ወስዳችሁ ስቀሉት አላቸው። አይሁድም መልሰው፦ እኛ ሕግ አለን፥ እንደ ሕጋችንም ሊሞት ይገባዋል፥ ራሱን የእግዚአብሔር ልጅ አድርጎአልና አሉት።*

*(የዮሐንስ ወንጌል 19:6-7)*

የስቅለት ታሪክ የሚጀምረው በብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ነው (መዝሙር 22፡12-18፣ ኢሳይያስ 53፣ ዘካርያስ 12፡10)፡፡ ኢየሱስም እንዴት እንደሚሞትና ለምን ዓላማ እንደሚሞት በተደጋጋሚ ግልፅ አድርጎ ተናግሯል፡፡

> *"እንዲሁም የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም።" (ማቴዎስ 20፡28)*
>
> *"ሙሴም በምድረ በዳ እባብን እንደ ሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ይገባዋል። በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።" (ዮሐንስ 3፡14-16)*
>
> *"መልካም እረኛ እኔ ነኝ። መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል።" (ዮሐንስ 10፡11)*
>
> *"ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ ባረከ ቈርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና፦ እንካችሁ፥ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው አለ። ጽዋንም አንሥቶ አመስግኖም ሰጣቸው እንዲህም አለ፦ ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ፤ ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው።" (ማቴዎስ 26፡26-28)*

መሲሁ እንዴትና ለምን እንደሚሞት ነቢያት በግልፅ ተናግረው፣ ኢየሱስ ራሱ ይህንኑ አረጋግጦ፣ ሐዋርያቱም የሞቱን ዓላማ በመተንተን አስተምረው ሲያበቁ "አይሁድ ስለፈለጉ ብቻ ነው የሞተው፤ በቃ አለቀ" ብሎ ማለት አስቂኝ ነው፡፡ በዚህ ታሪክ ውስጥ የአይሁድ መሪዎች እግረ መንገድ የገቡ ተዋንያን እንጂ ጀማሪዎችም ደምዳሚዎችም አይደሉም፡፡ በስቅለት ሒደት ውስጥ የተለያየ የልብ ምኞት የነበራቸው ወገኖች ተሳትፈዋል፤ አይሁድ በቅንዓት፣ ይሁዳ ለገንዘብ፣ ሮማውያን አመፅ እንዳይነሳ በመፍራት፣ ወዘተ.፡፡ ነገር ግን የታሪኩ ጀማሪም ሆነ ፈፃሚ ልዑል እግዚአብሔር ነው፡፡



4. <u>ከስተቱ አንድ ሲሆን ምልከታው ግን ይለያያል</u>

- ሮማውያን ስቅለቱን **ለሀገር ክህደት** ወንጀል የተላለፈ ቅጣት እንደሆነ ያምናሉ
- አይሁዳውያን ደግሞ **ለሀይማኖት ክህደት የተፈጸመ ቅጣት** አድርገው ይወስዱታል።
- ኢየሱስ ደግሞ ከደቀመዛሙርቱ መካከል አንዱ አሳልፎ በመስጠቱ ሳቢያ የተፈጸመ **ግድያ** እንደሆነ ያምናል።
- ክርስቲያኖች ደግሞ **ለሀጥያታቸው ማስተሰሪያ** የተደረገ መስዋዕትነት እንደሆነ ያምናሉ።

**ታዲያ የትኛው ነው ትክክል?**

ኢየሱስ ስለ ኃጢአታችን ስርየት ሲል እንደሚሞት በግልፅ ስለተናገረ ደራሲው የኢየሱስን አመለካከት በተመለከተ ሐሰተኛ መረጃን አስተላልፏል፦

> *"ሙሴም በምድረ በዳ እባብን እንደ ሰቀለ እንዲሁ <u>በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ይገባዋል።</u> በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።" (ዮሐንስ 3፡14-16)*

*ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ ባረከ ቈርሶም ሰጣቸውና፡- እንካችሁ፤ ይህ ሥጋዬ ነው አለ። ጽዋንም አንሥቶ አመስግኖም ሰጣቸው፥ ሁሉም ከእርሱ ጠጡ። እርሱም፡- ይህ ስለ ብዙዎች የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ነው።" (ማርቆስ 14፡22-24)*

ኢየሱስ ስለ ኃጢአታችን ስርየት ሲል እንደሚሞት በመናገሩ ምክንያት እምነታችን ከኢየሱስ ትምሕርት ጋር የሚስማማ ነው፡፡ ሲቀጥል ሮማውያንም ሆኑ አይሁድ የፈለጉትን ቢያስቡ ዋናው ነጥብ የእግዚአብሔር ዓላማ ተፈፃሚ መሆኑ ነውና ምንም የሚያመጣው ለውጥ የለም፡፡ ሙግቱ ከሚጠበቀው በታች ገለባ ነው፡፡

5. <u>የኢየሱስ መደበቅ</u>

ኢየሱስ ከአይሁዳውያን ቅጣት ለማምለጥ በማሰብ በተለያዩ ጊዜያት ይደበቃቸው ነበር። በዚህም ምክንያት ትክክለኛውን መረጃ ማግኘት ባለመቻላቸው ነበር ይሁዳን መረጃ እንዲሰጣቸው መደለያ የከፈሉት።

*" ወደ ቤቱም ሰደደውና፡- ወደ መንደሩ አትግባ በመንደሩም ለማንም አንዳች አትናገር አለው።"*

*(የማርቆስ ወንጌል 8:26)*

*"ስለ እርሱም ለማንም እንዳይናገሩ አዘዛቸው።"*

*(የማርቆስ ወንጌል 8:30)*

**ኢየሱስ ወደዚህ ምድር የመጣበት ዋነኛ አለማ ለሰው ልጆች ሀጥያት መሠቀል ከነበረ ለምን ይደበቃል? መሸሸስ ለምን አስፈለገው?**

“ለሁሉ ጊዜ አለው፡፡” የደራሲው ሙግት በነዚህ ሦስት ቃላት ውድቅ ሆኗል፡፡ ኢየሱስ ከመሞቱ በፊት የሞቱን ዓላማ ለዓለም የሚያስረዱና ትንሣኤውን የሚያውጁ ምስክሮችን ማዘጋጀት ነበረበት፡፡ ይህንን ካደረገ በኋላ ጊዜው ሲደርስ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ በራሱ ፈቃድ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፡-

*“ኢየሱስም ወደ ኢየሩሳሌም ሊወጣ ሳለ፥ በመንገድ አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ብቻቸውን ወደ እርሱ አቅርቦ፡- እነሆ፥ ወደ ኢየሩሳሌም እንወጣለን፥ የሰው ልጅም ለካህናት አለቆችና ለጻፎች ይሰጣል፤ የሞት ፍርድም ይፈርዱበታል፥ ሊዘባበቱበትም ሊገርፉትም ሊሰቅሉትም ለአሕዛብ አሳልፈው ይሰጡታል፥ በሦስተኛውም ቀን ይነሣል አላቸው።” (ማቴዎስ 20፡17-19)*

6. <u>ከስቅለት ይድን ዘንድ የእየሱስ ጸሎት</u>

እንደ ክርስቲያኖች እምነት መሰረት ኢየሱስ ወደዚህ ምድር የመጣበት ዋነኛ ዓላማ ለሰው ልጆች ተሰቅሎ ለሀጥያታችን ቤዛ ሊሆን ነው።

*" አሁን ነፍሴ ታውካለች ምንስ እላለሁ? አባት ሆይ፥ ከዚህ ሰዓት አድነኝ። ነገር ግን ስለዚህ ወደዚህ ሰዓት መጣሁ።"*

*(የዮሐንስ ወንጌል 12:27)*

*"ጥቂትም ወደ ፊት እልፍ ብሎ በፊቱ ወደቀና ሲጸልይ፦ አባቴ፥ ቢቻልስ፥ ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ፤ ነገር ግን አንተ እንደምትወድ ይሁን እንጂ እኔ እንደምወድ አይሁን አለ።"*

*(የማቴዎስ ወንጌል 26:39)*

*«ከእነርሱም የድንጋይ ውርወራ የሚያህል ራቀ፥ ተንበርክኮም፦ አባት ሆይ፥ብትፈቅድ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ እያለ ይጸልይ ነበር።» (የሉቃስ ወንጌል 22፡41-42)*

**እንደ ክርስቲያኖች አመለካከት መሰረት ኢየሱስ ወደዚህ ምድር የመጣው ተሰቅሎ ለሀጥያታችን ቤዛ ይሆን ዘንድ ነው። ይህ ከሆነ አላማው ታዲያ ይህ ሁሉ ልመናና ጸሎት ምንን በማስመልከት ነው? ሊሞት እንደመጣ አያውቅም? ወይንስ በመጨረሻ ሀሳቡን ቀይሯል?**

ኢየሱስ ሐሳቡን አልቀየረም፡፡ ነገር ግን የመስቀል መከራ እጅግ አሣቃቂ በመሆኑ ምክንያት ፍርሃት ተሰምቶታል፡፡ ኢየሱስ ፍፁም ሰው ሆኖ ወደ ምድር መምጣቱን እናስታውስ፡፡ ስለዚህ እንደ ማንኛውም ሰው ፍርሃቱን በጸሎት ለአባቱ አቅርቧል፡፡ ዳሩ ግን ደራሲው በጠቀሳቸው ጥቅሶች ውስጥ ወደዚህ ዓለም የመጣው ለዚያች ሰዓት መሆኑን በመናገርና የአብ ፈቃድ እንዲከናወን በመጸለይ ለሞት ራሱን አሳልፎ ሰጠ እንጂ ወደ ኋላ አልተመለሰም፡-

> *"ኢየሱስም የሚመጣበትን ሁሉ አውቆ ወጣና፦ ማንን ትፈልጋላችሁ አላቸው። የናዝሬቱን ኢየሱስን ብለው መለሱለት። ኢየሱስ፦ እኔ ነኝ አላቸው። አሳልፎ የሰጠውም ይሁዳ ደግሞ ከእነርሱ ጋር ቆሞ ነበር። እንግዲህ፦ እኔ ነኝ ባላቸው ጊዜ ወደ ኋላ አፈግፍገው በምድር ወደቁ። ደግሞም፦ ማንን ትፈልጋላችሁ? ብሎ ጠየቃቸው። እነርሱም፦ የናዝሬቱን ኢየሱስን አሉት። ኢየሱስ መልሶ፦ እኔ ነኝ አልኋችሁ፤ እንግዲህ እኔን ትፈልጉ እንደ ሆናችሁ እነዚህ ይሂዱ ተዉአቸው አለ፡፡" (ዮሐንስ 18፡4-8)*

7. <u>አምላክ ሁሌም ልመናውን ይሰማው ነበር።</u>

ዩሀንስ በወንጌሉ እንደሚገልፀው የእየሱስ ፀሎት ሁሌም ተቀባይነት ያለው ነበር። ይህንን አስመልክቶ እራሱ እየሱስ እንዲህ ይላል፡-

*ድንጋዩንም አነሡት፦ ኢየሱስም ዓይኖቹን ወደ ላይ አንሥቶ፦ አባት ሆይ፥ ስለ ሰማኸኝ አመሰግንሃለሁ። ሁልጊዜም እንድትሰማኝ አወቅሁ..(የዮሐንስ ወንጌል 11:41- 42)*

ታዲያ በዚህ አንቀፅ እንደተቀመጠው እየሱስ ፀሎቱ የሚሰማለት ከሆነ እንዳይሰቀል ያደረገው ፀሎት ምን ውሀ በላው? በሌላ ቦታ ደግሞ ጭራሽ ፀሎቱ ተሰምቶ እንደነበር ጳውሎስ ይናገራል።

*"እርሱም በስጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ፥ እግዚአብሔርንም ስለ መፍራቱ ተሰማለት፤"*

*(ወደ ዕብራውያን 5:7)*

ከሞት ወደ ሚያድነው አካል ፀሎት አድርጎ ፀሎቱ ከተሰማለት እየሱስ አልሞተም ነበር ማለት ነው።

ኢየሱስ ፅዋው ከእርሱ ያልፍ ዘንድ መጸለዩ እውነት ቢሆንም የጸሎቱ መቋጫ የአብ ፈቃድ ይከናወን ዘንድ በመሆኑ ጸሎቱ ተሰምቶ የአብ ፈቃድ ተከናውኗል፡፡

> *“ከእነርሱም የድንጋይ ውርወራ የሚያህል ራቀ፥ ተንበርክኮም፦ አባት ሆይ፥ ብትፈቅድ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ እያለ ይጸልይ ነበር።” (ሉቃስ 22፡41-42)*

ደራሲው ለዕብራውያን መጽሐፍ ፍጹም እንግዳ በሆነው እስላማዊ አመለካከት ከውጪ ተመልክቶ ጥቅሱን መተርጎሙ ስህተት ነው፡፡ የዕብራውያን መልእክት አጠቃላይ ሐሳብ የኢየሱስን ሞት አንድምታ መተንተን በመሆኑ ይህቺን አንዷን ጥቅስ ከመጽሐፉ አጠቃላይ ሐሳብ ነጥሎ ማየት ተገቢ አይደለም፡፡ የዕብራውያን ጸሐፊ ኢየሱስ መሞቱንና ከሞት መነሳቱን በተደጋጋሚ ጽፏል፡-

> *“እርሱም የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ ሆኖ፥ ሁሉን በስልጣኑ ቃል እየደገፈ፥ ኃጢአታችንን በራሱ ካነጻ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ፡፡” (ዕብራውያን 1፡3)*

> *“ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ ስለ ሰው ሁሉ ሞትን ይቀምስ ዘንድ፥ ከመላእክት ይልቅ በጥቂት አንሶ የነበረውን ኢየሱስን ከሞት መከራ የተነሣ የክብርና የምስጋናን ዘውድ ተጭኖ እናየዋለን። ብዙ ልጆችን ወደ ክብር ሲያመጣ የመዳናቸውን ራስ በመከራ ይፈጽም ዘንድ፥ ከእርሱ የተነሣ ሁሉ በእርሱም ሁሉ ለሆነ፥ ለእርሱ ተገብቶታልና።” (ዕብራውያን 2፡9-10)*

> *“እንግዲህ ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ፥ እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር፥ ይኸውም ዲያብሎስ ነው፥ በሕይወታቸውም ሁሉ ስለ ሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነጻ እንዲያወጣ፥ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ።” (ዕብራውያን 2፡14-15)*

> *“ቅዱስና ያለ ተንኮል ነውርም የሌለበት ከኃጢአተኞችም የተለየ ከሰማያትም ከፍ ከፍ ያለ፥ እንደዚህ ያለ ሊቀ ካህናት ይገባልና፤ እርሱም እንደነዚያ ሊቃነ ካህናት አስቀድሞ ስለ ራሱ ኃጢአት በኋላም ስለ ሕዝቡ ኃጢአት ዕለት ዕለት መሥዋዕትን ሊያቀርብ አያስፈልገውም፤ ራሱን ባቀረበ ጊዜ ይህን አንድ ጊዜ ፈጽሞ አድርጎአልና።” (ዕብራውያን 7፡26-27)*

*"እንግዲህ እነዚህን የሚያህሉ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን ካሉልን፥ እኛ ደግሞ ሸክምን ሁሉ ቶሎም የሚከበንን ኃጢአት አስወግደን፥ የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልከተን፥ በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ፤ <u>እርሱ ነውርን ንቆ በፊቱም ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሦ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአልና።"</u> (ዕብራውያን 12፡1-2)*

*"ስለዚህ <u>ኢየሱስ ደግሞ በገዛ ደሙ ሕዝቡን እንዲቀድስ ከበር ውጭ መከራን ተቀበለ።"</u> (ዕብራውያን 13፡2)*

*<u>"በዘላለም ኪዳን ደም</u> ለበጎች ትልቅ እረኛ የሆነውን <u>ጌታችንን ኢየሱስን ከሙታን ያወጣው</u> የሰላም አምላክ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በፊቱ ደስ የሚያሰኘውን በእናንተ እያደረገ፥ ፈቃዱን ታደርጉ ዘንድ በመልካም ሥራ ሁሉ ፍጹማን ያድርጋችሁ፤ ለእርሱ እስከ ዘላለም ድረስ ክብር ይሁን፤ አሜን።" (ዕብራውያን 13፡20-21*

በዕብራውያን ጸሐፊ መሠረት ኢየሱስ መከራን ተቀብሏል፣ ተሰቅሏል፣ ሞቷል፣ ከሙታን ተነስቷል፡፡ ስለዚህ ኢየሱስ ከሞት የዳነው ባለመሰቀልና ባለመሞት ሳይሆን ተሰቅሎ በመሞትና ሞትን ድል አድርጎ በመነሣት በትንሣኤው አማካይነት ነው፡፡ ሞትን ድል አድርጎ በመነሳቱ ከሞት ድኗል፡፡ ከዚህ የተለየ ትርጓሜ በዕብራውያን መጽሐፍም ሆነ በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ድጋፍ የለውም፡፡

8. <u>እየሱስን ሊያበረታ መልዐክ ወርዶ ነበር?</u>

በወንጌል እንደተገለጸው በመጨረሻዎቹ የኢየሱስ ጊዜያት ያበረታው ዘንድ መልዐክ ወርዶለት ነበር።

*ብትፈቅድ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ እያለ ይጸልይ ነበር። ከሰማይም መጥቶ የሚያበረታ መልአክ ታየው። (የሉቃስ ወንጌል 22፡42-43 )*

የዚህ መልዐክ ብርታት ማሳያው ምንድን ነበር? ከላይ እንደተመለከትነው እንዳይሞት ፀለየ ከዚያም መልዐክ ወርዶ አበረታው፤ በሌላ አነጋገር እየሱስ ይፀልየው ለነበረው ተማፅኖ አምላክ ምላሹን በመልዐኩ በኩል ልኳል ማለት ነው። የሱ ተማፅኖ ምላሽ ካገኘ ደግሞ በአጭር ቃል "አልተሰቀለም ነበር" ማለት ነው።

መልአኩ የመስቀል መከራውን በጽናት እንዲጋፈጥ ሊያበረታው ነው የመጣው፡፡ ደራሲው ያለ ማስረጃ በድርቅና እያወራ ነው፡፡ ከዚያ ቀጥሎ በሚገኙት ጥቅሶች ውስጥ "በወታደሮች ተያዘ፤ ተሰቀለ" የሚለውን ክፍል በግብር አባቱ መቀስ ስለቆረጠው እንጂ ጥቅሱ ኢየሱስ መሰቀሉን በግልፅ ይናገራል፡-

"ከሰማይም መጥቶ የሚያበረታ መልአክ ታየው። በፍርሃትም ሲጣጣር አጽንቶ ይጸልይ ነበር፤ ወዙም በምድር ላይ እንደሚወርድ እንደ ደም ነጠብጣብ ነበረ። ከጸሎትም ተነሥቶ ወደ ደቀ መዛሙርቱ መጣና ከኀዘን የተነሣ ተኝተው ሲያገኛቸው፡- ስለ ምን ትተኛላችሁ? ወደ ፈተና እንዳትገቡ ተነሥታችሁ ጸልዩ አላቸው። <u>ገናም ሲናገር እነሆ፥ ሰዎች መጡ፤ ከአሥራ ሁለቱ አንዱም ይሁዳ የሚባለው ይቀድማቸው ነበር፥ ሊስመውም ወደ ኢየሱስ ቀረበ። ኢየሱስ ግን፡- ይሁዳ ሆይ፥ በመሳም የሰውን ልጅ አሳልፈህ ትሰጣለህን? አለው።</u> በዙሪያውም የነበሩት የሚሆነውን ባዩ ጊዜ፡- ጌታ ሆይ፥ በሰይፍ እንምታቸውን? አሉት። ከእነርሱም አንዱ የሊቀ ካህናቱን ባሪያ መትቶ

ቀኝ ጆሮውን ቈረጠው። ኢየሱስ ግን መልሶ፦ ይህንስ ፍቀዱ አለ፤ ጆሮውንም ዳስሶ ፈወሰው። ኢየሱስም ወደ እርሱ ለመጡበት ለካህናት አለቆችና ለመቅደስ አዛዦች ለሽማግሌዎችም፦ ወንበዴን እንደምትይዙ ሰይፍና ጐመድ ይዛችሁ ወጣችሁን? በመቅደስ ዕለት ዕለት ከእናንተ ጋር ስሆን እጃችሁን አልዘረጋችሁብኝም፤ ይህ ግን ጊዜያችሁና የጨለማው ሥልጣን ነው አላቸው። ይዘውም ወሰዱት ወደ ሊቀ ካህናት ቤትም አገቡት፤ ጴጥሮስም ርቆ ይከተለው ነበር። በግቢ መካከልም እሳት አንድደው በአንድነት ተቀምጠው ሳሉ ጴጥሮስ በመካከላቸው ተቀመጠ።" (ሉቃስ 22፡43-55)

"እነርሱ ግን እንዲሰቀል በታላቅ ድምፅ አጽንተው ለመኑት። የእነርሱ ጩኸትና የካህናት አለቆችም ቃል በረታ። ጲላጦስም ልመናቸው እንዲሆንላቸው ፈረደበት። ያንን የለመኑትንም፥ ስለ ሁከት ሰውንም ስለ መግደል በወኅኒ ታስሮ የነበረውን አስፈታላቸው፥ ኢየሱስን ግን ለፈቃዳቸው አሳልፎ ሰጠው። በወሰዱትም ጊዜ ስምዖን የተባለ የቀሬናን ሰው ከገጠር ሲመጣ ይዘው ከኢየሱስ በኋላ መስቀሉን እንዲሸከም ጫኑበት። ዋይ ዋይ ከሚሉና ሙሾ ከሚያወጡ ሴቶችና ከሕዝቡ እጅግ ብዙዎች ተከተሉት። ኢየሱስ ግን ወደ እነርሱ ዘወር ብሎ እንዲህ አለ፦ እናንተ የኢየሩሳሌም ልጆች፥ ለእኔስ አታልቅሱልኝ፤ ዳሩ ግን፦ መካኖችና ያልወለዱ ማኅፀኖች ያላጠቡ ጡቶችም ብፁዓን ናቸው የሚሉበት ጊዜ እነሆ ይመጣልና ለራሳችሁና ለልጆቻችሁ አልቅሱ። በዚያን ጊዜ ተራራዎችን፦ በላያችን ውደቁ፥ ኮረብቶችንም፦ ሰውሩን ይሉ ዘንድ ይጀምራሉ፤ በእርጥብ እንጨት እንዲህ የሚያደርጉ ከሆኑ፥ በደረቀውስ እንዴት ይሆን? ሌሎችንም ሁለት ክፉ አድራጊዎች ደግሞ ከእርሱ ጋር ይገድሉ ዘንድ ወሰዱ። ቀራንዮም ወደሚባል ስፍራ በደረሱ ጊዜ፥ በዚያ እርሱን ክፉ አድራጊዎቹንም አንዱን በቀኝ ሁለተኛውንም በግራ ሰቀሉ። ኢየሱስም፦ አባት ሆይ፥ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው አለ። ልብሱንም ተካፍለው ዕጣ ተጣጣሉበት። ሕዝቡም ቆመው ይመለከቱ ነበር። መኳንንቱም ደግሞ፦ ሌሎችን አዳነ፤ እርሱ በእግዚአብሔር የተመረጠው ክርስቶስ ከሆነ፥ ራሱን ያድን እያሉ ያፌዙበት ነበር።" (ሉቃስ 23፡23-35)

"ተሰቅሏል" ይልሃል፡፡ በድርቅና የምታመጣው ነገር የለም፡፡

9. ጲላጦስ ፍርዱን አዘግይቶት ነበር

ጲላጦስ ሆን ብሎ የስቅለቱ ጊዜ እንዲራዘምና ውሳኔ እንዳይሰጠው አዘግይቶት ነበር። ይህም ቀኑ ሰንበት በመሆኑ ምክንያት መስቀል ላይ

ለጥቂት ጊዜያት እንደሚቆይ ተረድቶ ነበር። የ33 አመት ወጣት የነበረው እየሱስ በመስቀል ላይ የቆየው ከ3-6 ለሚሆኑ ሰአታት ብቻ ነበር። አንድ ሰው በነዚህ አነስተኛ ጊዜያት ውስጥ የመሞት እድሉ በጣም የተመናመነ ነው። ስቅለቱ አካሉን ይጎዳው ይሆናል እንጅ መሞት የሚያደርስ አልነበረም። በሮማውያን የአገዛዝ ጊዜ በስቅለት ይሞቱ የነበሩ ሰዎች ቢያንስ ሁለት ቀን ይፈጅባቸው ነበር።

ጲላጦስ ኢየሱስ የሞት ፍርድ እንዳይፈረድበት ተሟግቷል፡፡ ነገር ግን አይሁድ አመፅ የማስነሳት ሐሳብ ስለነበራቸው ለሞት አሳልፎ ሰጥቶታል፡፡ በመስቀል ላይ መሞትን በተመለከተ እንደየተሰቃዩ ይለያያል፡፡ ተሰቃዩ ሰው አስቀድሞ ብዙ መከራ የደረሰበት ከሆነ በጥቂት ሰዓታት ውስጥ ሊሞት ይችላል፡፡ ሳይገረፍና ብዙ እንግልት ሳይደርስበት ከተሰቀለ ደግሞ ለመሞት ጊዜ ሊወስድበት ይችላል፡፡ ሆኖም አንድ ሰው ሳይሞት ከመስቀል ላይ የሚወርድ ከሆነ የመሞት ዕድሉ ከፍተኛ ነው፡፡

ለምሳሌ ያህል ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን ሦስት የሚያውቃቸው ሰዎች ተሰቅለው ስላያቸው ሮማውያንን በመማፀን ከመስቀል ላይ እንዲወርዱ እንዳደረጋቸው ጽፏል፡፡ በወቅቱ የነበረው ከፍተኛ የህክምና እርዳታ ቢደረግላቸውም ሁለቱ ወዲያውኑ ሲሞቱ አንዱ ብቻ ነበር መትረፍ የቻለው፡፡ በመስቀል ላይ ለአጭር ሰዓት እንኳ የተሰቀለ ሰው ሳይሞት ቢወርድ በዚያን ዘመን በነበረው ከፍተኛ የህክምና እርዳታ እንኳ የመትረፍ ዕድሉ ጠባብ ነው፡፡

10. <u>ጲላጦስ የዋለው ውለታ</u>

ጲላጦስ ኢየሱስን ነፃ ሰው ነው ብሎ በማሰብ ትልቅ ውለታ ሲውልለት ነበር። በሚስቱ ህልም ምክንያትም ያድነው ዘንድ ይጥር ነበር። ለዛም ነበር አይሁዶች ባይስማሙም ያለውን ልዩ መብት ሊጠቀም የሞከረው

*«እንግዲህ እነርሱ ተሰብስበው ሳሉ ጲላጦስ፡- በርባንን ወይስ ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን ማንኛውን ልፈታላችሁ ትወዳላችሁ? አላቸው፤ በቅንዓት አሳልፈው እንደ ሰጡት ያውቅ ነበርና።እርሱም በፍርድ ወንበር ተቀምጦ ሳለ ሚስቱ፡- ስለ እርሱ ዛሬ በሕልም እጅግ መከራ ተቀብያለሁና በዚያ ጻድቅ ሰው ምንም አታድርግ ብላ ላከችበት። የካህናት አለቆችና ሽማግሌዎች ግን በርባንን እንዲለምኑ ኢየሱስን ግን እንዲያጠፉ ሕዝቡን አባበሉ። ገዢውም መልሶ፡- ከሁለቱ ማንኛውን ልፈታላችሁ ትወዳላችሁ? አላቸው፤ እነርሱም፡- በርባንን አሉ። ጲላጦስ፡- ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን እንግዲህ ምን ላድርገው? አላቸው፤ ሁሉም፡- ይሰቀል አሉ።ገዢውም፡- ምን ነው? ያደረገው ክፋት ምንድር ነው? አለ፤ እነርሱ ግን፡- ይሰቀል እያሉ ጩኸት አበዙ። ጲላጦስም ሁከት እንዲጀመር እንጂ አንዳች እንዳይረባ ባየ ጊዜ፥ ውኃ አንሥቶ፡- እኔ ከዚህ ጻድቅ ሰው ደም ንጹሕ ነኝ፤ እናንተ ተጠንቀቁ ሲል በሕዝቡ ፊት እጁን ታጠበ።» ማቴዎስ 27፡17-24*

ይህንን የጲላጦስ ተግባር ለተመለከተ ሰው ኢየሱስን በግዴለሽነት እስከ መጨረሻው እንዳሰቀለው ለማሰብም ለመገመትም ይከብዳል።

ጲላጦስ ኢየሱስን ለማትረፍ የተቻለውን ያህል ተሟግቷል፡፡ ነገር ግን አይሁድ አመፅ ሊያስነሱ እንደሆነ ስለገባው ኢየሱስን አሳልፎ ሰጠ፡፡ ደራሲው ቆርጦ ያስቀረው ቀጣይ ጥቅስ እንዲህ ይላል፡- *"ሕዝቡም ሁሉ መልሰው፡- ደሙ በእኛና በልጆቻችን ላይ ይሁን አሉ። በዚያን ጊዜ በርባንን ፈታላቸው፥ **ኢየሱስን ግን ገርፎ ሊሰቀል አሳልፎ ሰጠ።**"* (ማቴ. 27፡17-24)

ጲላጦስ ከዚያ ቀደም አመፅ በመነሳቱ ምክንያት በቄሣር ዘንድ ተከስሶ በማስጠንቀቂያ ወደ ሥልጣኑ የተመለሰ ሰው ነበር፡፡ ድጋሜ በእርሱ ሰበብ አመፅ ቢነሳ የመጨረሻው ነበር፡፡ ስለዚህ በቄሣር ዘንድ ድጋሜ ተከስሶ ከሥልጣኑ በመባረርና ኢየሱስን አሳልፎ በመስጠት መካከል መምረጥ ነበረበት፡፡ ማንኛውም ስግብግብ ባለሥልጣን የሚፈፅመውን ተግባር ነበር የፈፀመው፡፡ በእስላማዊው የክህደት አስተምሕሮ ለታወረ ሰው ካልሆነ በስተቀር ይህ ለማሰብም ሆነ ለመገመት የሚከብድ ጉዳይ አይደለም፡፡

11. **የጲላጦስ ሚስት ህልም**

*"እርሱም በፍርድ ወንበር ተቀምጦ ሳለ ሚስቱ፡- ስለ እርሱ ዛሬ በሕልም እጅግ መከራ ተቀብያለሁና በዚያ ጻድቅ ሰው ምንም አታድርግ ብላ ላከችበት።" (የማቴዎስ ወንጌል 27:19)*

ይህ ህልም እንዴት ከእየሱስ ተልዕኮ በተቃራኒ ሊሆን ቻለ? እንደ ክርስትያኖች እምነት መሠረት የእየሱስ ዋነኛ ተልዕኮ ወደዚህ ምድር መጥቶ ለሰው ልጅ ሀጥያት መሞት ነው። የጲላጦስ ሚስት ህልም ግን ከዚህ ተልዕኮው በተቃራኒ ነበር። ይህ ህልምም በመፅሀፍ ቅዱስ ትልቅ ቦታ ተሰጥቶት ተዘግቦ እናገኘዋለን፤ በአንዳንድ የክርስትና የታሪክ መፅሀፍት ውስጥም ሴትየዋን እንደመልካም ሰው ተስላ እናገኛለን። ህልሙ ተራ ከነበረና ለታሪኩ ጠቃሚ ካልነበር በመጽሀፍ ቅዱስ የመዘገቡ ቁምነገር ምንድን ነው?

የኢየሱስ ንፅህና የጲላጦስ ሚስት ባየችው ሕልም መረጋገጡ ከኢየሱስ ተልዕኮ ጋር የሚጣረሰው እንዴት ሆኖ ነው? ኢየሱስ ስለ ኃጢአታችን ለመሞት የመጣ ቢሆንም ንፁህና ጻድቅ በመሆኑ ምክንያት ለሥልጣኑ ሲል ንፅህናውን እያወቀ አሳልፎ የሰጠው ጲላጦስን ጨምሮ በክፉ ሐሳብ በመነሳሳት እንዲገደል ያደረጉት ሰዎች በሙሉ በክፉ ሐሳባቸው ምክንያት ቅጣትን ይቀበላሉ፤ ተቀብለዋልም፡፡ ይህ ከኢየሱስ ተልዕኮ ጋር የሚፃረርበት ምንም ዓይነት መንገድ የለም፡፡

12. **የእግዚአብሄር ቁጣ**

የመሬት መንቀጥቀጥ፣ የፀሀይ ግርዶሽና መብረቅ የአምላክ ቁጣ ማሳያዎች ናቸው። ይህንን አስመልክቶ ለአብነት የዳዊትን ንግግር መጥቀስ እንችላለን

*" ምድርም ተንቀጠቀጠች ተናወጠችም፥ የተራሮችም መሠረቶች ተነቃነቁ፥ እግዚአብሔርም ተቈጥቶአልና ተንቀጠቀጡ።"*

*(መዝሙረ ዳዊት 18:7)*

እነዚህተግባራት ታዲያ በእየሱስ ስቅለት ወቅት ታይተው ነበር። ከዚህ የምንረዳው ነገር ተግባሩ አይደለም ለሰው ልጅ መዳኛ የተፈጸመ ተግባር ሊሆን ይቅርና አሳዛኝና አምላክን ያስቆጣ ጭምር እንደነበር ነው።


ይህ ሙግት በሦስት ምክንያቶች ውድቅ ነው፡፡

አንደኛ፡- የምድር መናወጥ በእግዚአብሔር ቁጣ ምክንያት ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር ክብር ሲገለጥ፣ መንፈስ ቅዱስ ሲወርድና የጌታ መልአክ ወደ ምድር ሲመጣ እንደተከሰተ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (ዘጸአት 19፡18፣ ዘኁልቁ 1፡5፣ የሐዋርያት ሥራ 4፡31፣ ማቴዎስ 28፡2)፡፡ ስለዚህ የምድር መናወጥ በመጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቁጣ መገለጫ ብቻ አይደለም፡፡

ሁለተኛ፡- ክርስቶስ ኃጢአታችንን በመሸከሙ ምክንያት እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ የሚያወርደውን ቁጣና መከራ እያስተናገደ ስለነበር የምድር መናወጡ በእግዚአብሔር ቁጣ ምክንያት የተከሰተ ነው ቢባል እንኳ የጠያቂው ሙግት ተቀባይነት የለውም፡፡

ሦስተኛ፡- እግዚአብሔር አንዲያ ልጁ ለዚያ ሁሉ ሥቃይ በመዳረጉ ምክንያት አዝኗል፤ እናም የምድር መናወጡ የእግዚአብሔርን ኀዘን የሚገልፅ ሊሆን ይችላል፡፡

በዚህም ሆነ በዚያ የጠያቂው ሙግት ውድቅ ነው፡፡



13. <u>የጲላጦስ መገረም</u>

*" ጲላጦስም አሁኑን እንዴት ሞተ ብሎ ተደነቀ፥ የመቶ አለቃውንም ጠርቶ ከሞተ ቆይቶአልን? ብሎ ጠየቀው፤"*

*(የማርቆስ ወንጌል 15:44)*

**ጲላጦስ የእየሱስ በመስቀል ላይ መሞት ሲነገረው በዚህ ፍጥነት እንዴት ሞተ? ሲል ተደንቋል። እንግዲህ ሁላችንም እንደምናውቀው ጲላጦስ በዚህ ዘርፍ እጅግ ልምድ ያለው ሰው ነበር፤ የሮማ ገዥዎች ሰዎችን በስቅላት መቅጣት የተካኑበት ተግባር ነው። ይህ ግርምቱ የመጣውም ከዚህ የተነሳ ነበር። አንድ የ33 አመት ያላገባ ወጣት በጥቂት ሰአታት ውስጥ እንደማይሞት ያቀዋል።**

ኢየሱስ መሞቱ ስለተረጋገጠ የጲላጦስ መገረም አለመገረም ምንም የሚያመጣው ለውጥ የለም፡፡ ኢየሱስ መሞቱ በቦታው በነበሩ ሰዎች ተረጋግጧል፡፡ ጠያቂው ጥቅሶችን በመቆራረጥ የተለየ ትርጉም ለመስጠት ቢሞክርም ቀጥለው የተቀመጡት ቃላት የኢየሱስን መሞት በግልፅ ይናገራሉ፡- *"ጲላጦስም አሁኑን እንዴት ሞተ ብሎ ተደነቀ፥ <u>የመቶ አለቃውንም ጠርቶ ከሞተ ቆይቶአልን? ብሎ ጠየቀው፤ **ከመቶ አለቃውም ተረድቶ በድኑን ለዮሴፍ ሰጠው።**</u>"* (ማርቆስ 15፡44-45)

ኢየሱስ በፈቃዱ ነፍሱን አሳልፎ መስጠቱን ማስታወስም አስፈላጊ ነው፡፡ ኢየሱስ በፈቃዱ ነፍሱን መስጠቱን መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይናገራል፡-

> "ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ ጮኸ <u>ነፍሱንም ሰጠ</u>።" (ማርቆስ 15፡37)
>
> "ኢየሱስም ሁለተኛ በታላቅ ድምፅ ጮኾ ነፍሱን ተወ።" (ማቴዎስ 27፡50)
>
> "ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ ጮኾ፡- አባት ሆይ፥ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ አለ። ይህንም ብሎ <u>ነፍሱን ሰጠ</u>።" (ሉቃስ 23፡46)
>
> "ኢየሱስም ሆምጣጤውን ከተቀበለ በኋላ፡- ተፈጸመ አለ፥ ራሱንም አዘንብሎ <u>ነፍሱን አሳልፎ ሰጠ</u>።" (ዮሐንስ 19፡30)

ኢየሱስ ፈቅዶ ነው ነፍሱን የሰጠው ስለዚህ ቶሎ መሞቱ አስገራሚ አይደለም፡፡

## 14. አብረውት የተሰቀሉት ወንበዴዎች

እየሱስ ሲሰቀል አብረው ተሰቅለው የነበሩ ሁለቱ ወንበዴዎች አልሞቱም ነበር። በዛም ምክንያት ወታደሮቹ እግሮቻቸውን ሰብረዋቸዋል።

*"ጭፍሮችም መጥተው የፊተኛውን ጭን ከእርሱም ጋር የተሰቀለውን የሌላውን ጭን ሰበሩ፤" (የዮሐንስ ወንጌል 19:32)*

**አብረውት የተሰቀሉት ግለሰቦች ሳይሞቱ ኢየሱስ እንዴት ሊሞት ይችላል? የተለየ ፍርድ እሱ ጋር ቢኖር ምናልባት ልንጠረጥር እንችል ይሆናል። ነገር ግን ሁሉም አብረውት የተሰቀሉ ተመሳሳይ ቅጣት የሚፈጸምባቸው ግለሰቦች ናቸው።**

አንደኛ፡- ኢየሱስ አስቀድሞ እንደተገረፈና ብዙ እንግልት እንደደረሰበት ተዘግቧል፡፡ የሮማውያን ግርፋት እጅግ አሠቃቂ ከመሆኑ የተነሳ ብዙ ሰዎች ከመሰቀላቸው በፊት ይሞቱ እንደነበር ታሪክ ይናገራል፡፡

ሁለተኛ፡- አንድ ሰው በመስቀል ላይ ሲሆን አየር ለማስገባት እግሮቹን ማጠፍና አየር ለማስወጣት ደግሞ በእግሮቹ ውስጥ በተሰኩት ሚስማሮች ላይ ቆሞ እግሮቹን መወጠር ያስፈልገዋል፡፡ ከኢየሱስ ጋር የነበሩትን ወንበዴዎች ጭኖች የሰበሩት አየር ማስወጣት ስለማይችሉ ወዲያውኑ እንዲሞቱ ነበር፡፡ ተሰቃዮች በእጆቻቸውና በእግሮቻቸው ላይ የተሰኩት ሚስማሮች የሚያደርሱባቸውን የህመም ሥቃል መቋቋም ይችሉ ዘንድ አደንዛዥ መጠጥ ይሰጣቸዋል፡፡ ይህ ደግሞ ሥቃያቸውን ስለሚስታግስ በቂ ትንፋሽ እንዲወስዱ ያግዛቸዋል፡፡ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ባልተለመደ ሁኔታ መጠጡን ስላልተቀበለ በሥቃዩ ምክንያት ለመተንፈስ መቸገሩ የሞቱን ጊዜ ማፋጠኑ እሙን ነው (ማርቆስ 15፡23)፡፡

ሦስተኛ፡- ሮማውያን የአንድን ሰው በመስቀል ላይ መሞት ለማረጋገጥ ወይንም ሞቱን ለማፍጠን የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ ከእነዚህ መካከል አንዱ በወንበዴዎቹ እንዳደረጉት ጭንን መስበር ሲሆን ሌላው ደግሞ በኢየሱስ እንዳደረጉት ልብ አካባቢ በጦር መውጋት ነው፡፡ ኢየሱስ ከመስቀል ሥቃይ ተርፏል ቢባል እንኳ ከጦር ውጋቱ ሊተርፍ አይችልም፡፡

አራተኛ፡- ከዚህ ሁሉ ሊተርፍ ይችላል ተብሎ ቢታሰብ እንኳ (ፈፅሞ ሊታመን የማይችል ቢሆንም) የአይሁድ የአገናነዝ ሥርዓት እንኳንስ ከመስቀል ላይ የወረደ ሰው ይቅርና ደህናውን ሰው እንኳ መግደል የሚችል ነው፡፡ እንደ ሲሚንቶ በሚያጣብቅ 100 ፓውንድ ቅመም ታሽጎ ከሞት መትረፉ የማይታመንም የማይታሰብም ነው፡፡

15. <u>ደምና ውሃ</u>

ወታደሩ የእየሱስን ጎን ሲወጋው ደምና ውሃ ወጥቶት ነበር፤ ይህ ደግሞ በህይወት እንደነበር የሚያረጋግጥልን ክስተት ነው። አንድ ሰው

ሲሞት ደሙ ወዲያውኑ ይረጋል። ደሙ ግፊት ኖሮት መፍሰስ ቻለ ማለት ግን የልብ ምቱ ነበረ ማለት ነው።

*"ነገር ግን ከጭፍሮች አንዱ ጎኑን በጦር ወጋው፤ ወዲያውም ደምና ውኃ ወጣ።" (የዮሐንስ ወንጌል 19: 34)*

**በጸሀፊው ዘገባ ውስጥ ደም መውጣቱን የሚገልፀው ክፍል ለምን ትኩረት ተሰጥቶት ሊዘገብ ቻለ? የሚለው ጥያቄ እዚህ ጋር መሠረታዊ ይሆናል።**

" ስለ እነዚህም የመሰከረ ይህንንም ጽፎ ያለ ይህ ደቀ መዝሙር ነው፥ ምስክሩም እውነት እንደ ሆነ እናውቃለን።"

(የዮሐንስ ወንጌል 21: 24)

**ጸሀፊው ከምንም በላይ በምስክርነቱ ተዓማኒነት ዙሪያ ትኩረት ሲያደርግ እናስተውላለን። ይህም ማለት የደም መውጣቱን ታሪክና መሠል መግለጽ ያሉበትን ምስክርነቶች መሸሸግ አልፈለገም ማለት ነው።**

ጠያቂው ዮሐንስ ምስጢራዊ በሆነ ኮድ የሆነ ዓይነት መልእክት እያስተላለፈልን እንደሆነ ለማስመሰል ጥረት ቢያደርግም ነገሩ ሁሉ ግልፅ ነው፡፡ ዮሐንስ የኢየሱስን መሞት እንዳንጠራጠር አስረግጦ እየነገረን ነው፡፡ በሕይወት ነበረ ቢባል እንኳ ጎኑ በጦር መወጋቱ ብቻውን ለሞት ይዳርገዋል፡፡ ጠያቂው ከተናገረው በተጻራሪ ከጎኑ ደምና ውኃ መፍሰሱ የኢየሱስን መሞት መቶ በመቶ ያረጋገረጠ ዘገባ ነው፡፡ የሞተ ሰው ልቡ አካባቢ ከተወጋ የተጠራቀመ ደም ይፈስሳል፡፡ ወታደሩ ኢየሱስን ሲወጋው ደም ብቻ ሳይኾን ደምና ውኀ ተለያይቶ ነበር የፈሰሰው፡፡ ይህ በሁለት ምክንያቶች ሊከሰት ይችላል፡፡ የመጀመርያው ሰው ሲሞት ደም ስለሚረጋ ከውኀ ይለያል፡፡ ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ልብ አካባቢ ውኀ መሳይ ፈሳሽ (ካባቤ ልብ) ስላለ የሞተ ሰው ሲወጋ ይህ ፈሳሽ ከደም ተለይቶ ይወጣል፡፡ በዚህም ሆነ በዚያ ደምና ውኀ መውጣቱ የኢየሱስን መሞት መቶ በመቶ ያረጋገጠ ክስተት ነበር፡፡ (Nabil Qureshi: *Seeking Allah, p. 150)*

ይህንን ጉዳይ ያጠኑ የጤና ተመራማሪዎች የጥናታቸውን ውጤት ማርች 21፣ 1986 ዓ.ም. በታተመው *Journal of the American Medical Association* ላይ ያሰፈሩ ሲሆን ደምና ውኀ መውጣቱ ኢየሱስ በጦር ከመወጋቱ በፊት መሞቱን መቶ በመቶ ያረጋገጠ ክስተት መኾኑን አረጋግጠዋል፡፡ ድምዳሜያቸውን እንዲህ ነበር ያስቀመጡት፡-

"Clearly, the weight of historical and medical evidence indicates that Jesus was dead before the wound to his side was inflicted and supports the traditional view that the spear thrust between his right rib, probably perforated not only the right lung but also the pericardium and heart and thereby ensured his death.

Accordingly, interpretations basedon the assumption that Jesus did not die on the cross appear to be at odds with modernmedical knowledge." *Journal of the American Medical Association* (21 March 1986) [1463]

ጠያቂው የመረጃ እጥረት እንዳለበት ግልፅ ነው፡፡

16. <u>ለሞቱ ማረጋገጫ</u>

ወታደሮቹ የኢየሱስን መሞትና አለመሞት ለማረጋገጥ ለምን ጎኑን መውጋት አስፈለጋቸው? ሌላ አይነት የማወቂያ መንገድ አልነበረምን?

መሞትና አለመሞቱን ለማረጋገጥ ጎኑን መውጋታቸው በጭራሽ ስሜት የሚሰጥ ነገር አይደለም። ምናልባት ከዚህ ውጭ ሌላ አማራጭ ሲጠቀሙ ካልነበረና ብቸኛ ማረጋገጫቸው ይህ ከነበረ ሊያስኬድ ይችላል። ለምንስ ያንን ተግባር ፈጸሙ? መሞት አለመሞቱን ለማወቅ ከተባለ ሌሎች አብረውት የተሰቀሉትንም በተመሳሳይ ጎናቸውን መውጋት ነበረባቸው። ይህ በታሪኩ ውስጥ የተጨመረ የተዛነፈ ትርክት እንደሆነ በቂ ማሳያ ነው።

ጠያቂው ቀደም ሲል ጎኑ ተወግቶ ደምና ውኃ መፍሰሱን ኢየሱስ አለመሞቱን ለማሳየት እንደ ማስረጃ መጥቀሱን እናስታውስ፡፡ አሁን ደግሞ ሐሳቡን በመቀየር ጎኑ በጦር የመወጋቱን ዘገባ ለማጣጣል ይሞክራል፡፡ ለማንኛውም ለዚህ ጥያቄ ሦስት ምላሾች አሉን፦

አንደኛ፦ በዚያን ዘመን ሮማውያን በመስቀል ላይ የተሰቀሉ ሰዎች መሞታቸውን ለማረጋገጥ ይጠቀሙባቸው ከነበሩት መንገዶች መካከል አንዱ በጦር መውጋት ነበር፡፡ በዘመኑ ይጠቀሟቸው ከነበሩት የማረጋገጫ መንገዶች መካከል አንዱን መጠቀማቸው እንዴት ቢሆን ነው ለጠያቂው ስሜት ያልሰጠው? ይህ በቦታው ላይ የነበሩት ሰዎች የግል ምርጫ በመሆኑ የእርሱ አስተያየትም ሆነ ስሜት ዋጋ የለውም፡፡

ሁለተኛ፦ ኢየሱስ አስቀድሞ ሞቶ ስለነበር ከጎኑ እንደተሰቀሉት ሰዎች ጭኑን መስበር አስፈላጊ አልነበረም፦

> <u>"ወደ ኢየሱስ በመጡ ጊዜ ግን እርሱ ፈጽሞ እንደ ሞተ አይተው ጭኑን አልሰበሩም፤</u> ነገር ግን ከጭፍሮች አንዱ ጎኑን በጦር ወጋው፤ ወዲያውም ደምና ውኃ ወጣ።" (ዮሐንስ 19፡33-34)

ሦስተኛ፦ አጥንቶቹ እንደማይሰበሩ አስቀድሞ ትንቢት ስለተነገረ ትንቢቱ መፈፀሙ ግድ ነበር፡፡

> "ይህ የሆነ፦ ከእርሱ አጥንት አይሰበርም የሚል የመጽሐፉ ቃል እንዲፈጸም ነው።" (ዮሐንስ 19፡36)

የክርስቶስ ምሳሌ የሆነው የፋሲካው በግ አጥንት እንዳይሰበር እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ውስጥ ትዕዛዝን በመስጠቱ ምክንያት የክርስቶስ አጥንት ቢሰበር ኖሮ የፋሲካውን መሥዋዕት መሥፈርት ስለማያሟላ ቤዛችን መኾን ባልቻለም ነበር

(ዘጸአት 12፡46፣ ዘኊልቁ 9፡12፣ 1ቆሮንቶስ 5፡7)፡፡ ስለዚህ የክርስቶስ አጥንት አለመሰበሩ የእግዚአብሔር ቅድመ ውሳኔ ነበር፡፡

17. <u>የእየሱስ ጭኖች አልተሰበሩም ነበር።</u>

*"ወደ ኢየሱስ በመጡ ጊዜ ግን እርሱ ፈጽሞ እንደ ሞተ አይተው ጭኑን አልሰበሩም፤" (ዮሐ 19: 33)*

**ከጥግ የነበሩት ሁለቱ ሳይሞቱ ኢየሱስ መሞቱ የሚገርም ከመሆኑ በተጨማሪ የጭኑ አለመሰበር ደግሞ ይበልጥ ጥያቄ ያጭራል። ጭኑ ያልተሰበረው ስለሞተ ከሆነ አንደኛው ወታደር ጎኑን መውጋት ለምን አስፈለገው? ሙቷል ብለው ጭኑን ካልሰበሩት መልሰው የሚወጉበትስ ምክንያት ምንድን ነው?**

ይህንን ጥያቄ አስቀድመን መልሰናል፡፡ በመስቀል ላይ የተሰቀለ ሰው አየር ለማስወጣትና ለማስገባት እግሮቹን ማንቀሳቀስ ስለሚያስፈልገው የእግሮቹን እንቅስቃሴ ብቻ በማየት መሞት አለመሞቱን መናገር ይቻላል፡፡ ኢየሱስ ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ እያሳየ ስላልነበር መሞቱ ግልፅ ነበር፤ ነገር ግን ጎኑን በጦር የወጉት ስለመሞቱ ምንም ዓይነት ጥርጣሬ እንዳይኖር ነው፡፡ ፀጉር መሰንጠቅ የሚፈልግ ሐያሲ ምንም ያህል የማስረጃ ብዛት ቢቀርብለት አቃቂር ማውጣቱ አይቀርም፡፡

18. <u>እየሱስ በመቃብር ውስጥ አልተቀበረም ነበር።</u>

እንደሚታወቀው የአይሁዳውያኑ የሺህ አመታት ልማድ አንድ ሰው በሚሞትበት ሰዓት መሬት ቆፍሮ መቅበር ነው። እየሱስ ግን እንደዛ አልተቀበረም። የወሰዱት አየር ያለበትና ሰፋ ያለ ክፍል ውስጥ ነበር። ይህ ደግሞ እየሱስ በመስቀል ላይ እንዳልሞተ ያውቁ እንደነበር በቂ ማሳያ ነው። አፈር ቆፍረው ቢቀብሩት እንደሚሞት ያቃሉ ስለዚህ የተሻለው አማራጭ ሰፋ ያለ ቤት ውስጥ በማስገባት እስትንፋሱን ማቆየት ነው።

ጠያቂው ስለ አይሁድ የቀብር ሥነ ስርዓት ምንም ዕውቀት የሌለው ሰው ነው፡፡ የጥንቶቹ አይሁድ፣ በተለይም በክርስቶስ ዘመን የነበሩት መሬት በመቆፈር ሳይሆን ዋሻዎችን በመፈልፈል ነበር አስክሬኖችን ይቀብሩ የነበሩት፡፡ ለዚህ ማስረጃ የሚሆኑ እስከ ዛሬ ድረስ በኢየሩሳሌም ዙርያና በምድረ እስራኤል የሚታዩ ዋሻዎች አያሌ ናቸው፡፡ የመጀመርያው ክፍለ ዘመን አይሁድ የዘመዶቻቸው አጥንት እስከ ዕለተ ትንሣኤ ተጠብቆ መቆየት እንዳለበት ያምኑ ስለነበር እንዲበላሹ አይፈልጉም፤ ስለዚህ መሬት በመቆፈር ሳይሆን በዋሻ ውስጥ ነበር ይቀብሩ የነበሩት፡፡ የሚኞች አስክሬን ስጋ ከረገፈ በኋላ አጥንቶቹን በትንንሽ ሳጥኖች (Ossouri) ውስጥ ያስቀምጣሉ፡፡ ለበለጠ መረጃ <u>እዚህ</u> እና <u>እዚህ</u> ጋ በመንካት በምሑራን የተጻፉ ጽሑፎችን ያንብቡ፡፡

የኢየሱስ ወዳጅ አልዓዘር በሞተ ጊዜ በተመሳሳይ ዋሻ ውስጥ ነበር የተቀበረው፡፡

"ኢየሱስም በራሱ አዝኖ ወደ መቃብሩ መጣ፤ እርሱም ዋሻ ነበረ፤ ድንጋይም ተገጥሞበት ነበር።" (ዮሐ. 11፡38)

አልዓዘር ስላልሞተ ይሆን በዋሻ ውስጥ የቀበሩት? ደራሲው ማስረጃ የሌለው የግል ፈጠራውን እያስነበበን ነው፡፡

> **19. <u>መሞቱን ማን እርግጠኛ መሆን ይችላል?</u>**
>
> እንደ መጽሀፍ ቅዱስ ገለጻ እየሱስ በሞተበት ወቅት ከፍተኛ የመሬት መንቀጥቀጥና የመብረቅ ብልጭታ ነበር። በተጨማሪም የጸሀይ ግርዶሽ ሳይቀር ተከስቶ ነበር። በዚህ ሰዓት ሊፈጠር የሚችለውና መደናበርና ሩጫ ማንም የሚገምተው ነው። ይህ መብረቅና የመሬት መንቀጥቀጥ ያደናበረው ህዝብ እየሱስ ለመሞቱ እንደማስረጃ የሚቀርብ አይደለም። እርሱ በተሰቀለበት ሰዓት እነርሱ ነፍሳቸውን ለማዳን ሲሸሹ ነበር። ታዲያ ማነው ከመነሻው እስከመጨረሻው በቦታው በሞሆን የአይን ምስክር ሊሆን የሚችለው? የለም

የፀሐይ መጨለምና የምድር መናወጡ እንደተከሰተ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፏል (ማቴዎስ 27፡50-51)፤ ነገር ግን የመብረቅ ብልጭታውንና ነፍሳቸውን ለማዳን የሚሸሹ ሰዎችን ትርምስ ጠያቂው ፊልም ውስጥ ዐይቶት እንደሆን እንጂ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልተጻፈም፡፡ ይህ ሁሉ ነገር ሲከሰት የኢየሱስ የቅርብ ተከታዮችና ቤተሰቦች እንዲሁም የሮማ ወታደሮችም በመስቀሉ አጠገብ ነበሩ፡፡ እነዚህ ወገኖች በመስቀል ላይ ሲሞት ዐይተውታል፣ መሞቱን ለማረጋገጥ ወታደሮች ጎኑን በጦር ወግተውታል፣ ወዳጆቹ ሥጋውን ከመስቀል ላይ አውርደዋል፣ ገንዘውታል፣ ቀብረውታል (ማቴዎስ 27፡45-61፣ ማርቆስ 15፡27-47፣ ሉቃስ 23፡44-56፣ ዮሐንስ 19፡25-42)፡፡ በግርግሩ መካከል የሆነ ነገር ተፈጥሯል ከተባለ ይህንን ሁሉ ሲያደርጉ ኢየሱስ መሆኑን አላወቁም ነበር ማለት ነው? ምን የሚሉት ቅዠት ነው!

> **20. <u>ድንጋዩ በቦታው አልነበረም</u>**
>
> ከሞት ለተነሳ አካል ይወጣ ዘንድ ድንጋይ አያግደውም። ድንጋይ አንፏቆ መውጣትም አይጠበቅበትም። ነገር ግን ያልሞተ የተለመደ ሰው አካል ከሆነ ግን ድንጋይ አንስቶ መውጣት ይኖርበታል። በዚህ መልኩ ካየነው እየሱስ እንዳልሞተ እንረዳለን። መግደላዊት ማርያም ልትነካው ባለች ጊዜም «አትንኪኝ»ብሎ ሲከለክላት እናስተውላለን።
>
> *««ኢየሱስም፦ ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ፤ ...»*
>
> *የሀንስ 20፡17*
>
> **ጥያቄው ለምን አትንኪኝ አላት? ገና አላረግሁም ሲልስ በትክክል ምን ማለቱ ነበር? ገና አለመሞቱን (ነፍሱ ወደ አባቱ አለመሄዱን) እና አካሉ የቀድሞው ያልሞተው አካሉ እንደሆነ መግለጹ ነበር።**

ድንጋዩ የተንከባለለው ኢየሱስ ከመቃብር ይወጣ ዘንድ እንደነበር በወንጌላት አልተዘገበም፡፡ ነገር ግን ድንጋዩን ማን አንከባለለው ለሚለው ጥያቄ መጽሐፍ ቅዱስ ምላሽ ይሰጠናል፡-

> “እነሆም፥ <u>የጌታ መልአክ ከሰማይ ስለ ወረደ ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ፤ ቀርቦም ድንጋዩን አንከባሎ በላዩ ተቀመጠ።</u> መልኩም እንደ መብረቅ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ ነበረ። ጠባቆቹም እርሱን ከመፍራት የተነሣ

ተናወጡ እንደ ሞቱም ሆኑ። መልአኩም መልሶ ሴቶቹን አላቸው። እናንተስ አትፍሩ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንድትሹ አውቃለሁና፤ እንደ ተናገረ ተነሥቶአልና በዚህ የለም፤ የተኛበትን ስፍራ ኑና እዩ። ፈጥናችሁም ሂዱና፦ ከሙታን ተነሣ፥ እነሆም፥ ወደ ገሊላ ይቀድማችኋል በዚያም ታዩታላችሁ ብላችሁ ለደቀ መዛሙርቱ ንገሩአቸው። እነሆም፥ ነገርኋችሁ።" (ማቴዎስ 28፡2-7)

ስለዚህ ድንጋዩን ያንከባለለው የጌታ መልአክ ሲሆን መቃብሩ ባዶ መሆኑን ማረጋገጫ ለመስጠት እንጂ ኢየሱስ ከመቃብሩ እንዲወጣ አልነበረም፡፡

መግደላዊ ማርያምን ለምን አትንኪኝ አላት? ምላሹ እዚያው ላይ ተቀምጧል፡-

*"ኢየሱስም፦ ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ፤ ነገር ግን ወደ ወንድሞቼ ሄደሽ፦ እኔ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ ዓርጋለሁ ብለሽ ንገሪአቸው አላት።"*

ጠያቂው እንደተረጎመው "ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ" ማለቱ "አልሞትኩም ወይም ነፍሴ ወደ አባቴ አልሄደችም" ማለት ከሆነ "ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ ዓርጋለሁ ብለሽ ንገሪአቸው" ብሎ ሲል "እሞታለሁ" እያለ ነበር ማለት ነው? ትርጉም አይሰጥም፡፡ በየትኛውም አገር ቋንቋ እርገትና ሞት የተለያዩ ሁለት ነገሮች ናቸው፡፡ ሞቶ ነፍሱ የወጣች ሰው "ሞተ፣ አረፈ፣ አንቀላፋ፣ ነፍሱ ወደ ጌታ ሄደች፣ ወዘተ." ይባላል እንጂ "አረገ" አይባልም፡፡ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቶ ከመታየቱ አስቀድሞ ወደ አብ ስለማረጉ እንጂ ስለመሞቱ እየተናገረ አይደለም፡፡

ጆሽ ማክዱዌል ከአሕመድ ዲዳት ጋር ባደረጉት ክርክር ወቅት ይህ ጥያቄ ተነስቶ እንዲህ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡-

> "አትንኪኝ" ሲል "ስለሚያመኝ – አትንኪኝ" ማለት እንደሆነ ሚስተር ዲዳት ተናግረዋል፡፡ መልካም፤ ሚስተር ዲዳት ተከታዩን ሐረግ እባክዎትን ያንብቡ፡፡ እንዲህ ይላል "ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ፡፡" ለዚያ ነው ሊነኩት ያልተገባው፤ ምክንያቱን ሲገልፅ "ገና ወደ አባቴ አላረግሁም" ብሏል፡፡ ከዚያ እንደዚህ አለ፡- "ነገር ግን ወደ ወንድሞቼ ሄደሽ ‹ወደ አባቴ  አርጋለሁ› ብሏል ብለሽ ንገሪያቸው፡፡" ከጥቂት ጊዜ ቆይታ በኋላ ደግሞ "ልትነኩኝ ትችላላችሁ፡፡ እግሮቼን ንኩ" አለ፡፡ ለምንድነው እንደርሱ ያደረገው? ኦ! ክቡራትና ክቡራን፤ ይህ በጣም ውብ ከሆኑ ነገሮች መካከል አንዱ ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን እንደተነገረው፤ በድንኳኑ ውስጥ የአይሁድ ሊቀ ካህን መሥዋዕቱን ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ይወስዳል፡፡ ሕዝቡም በውጪ ይጠብቃሉ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር መሥዋዕቱን ካልተቀበለ ካህኑ ተቀስፎ እንደሚሞት ያውቃሉና፡፡ ሊቀ ካህኑ ተመልሶ እንስኪመጣ በጉጉት ይጠብቁታል፡፡ እናም ሊቀ ካህኑ ተመልሶ ሲመጣ ሁሉም ሰው በደስታ ይጮሃል! ምክንያቱ "እግዚአብሔር መሥዋዕታችንን ተቀብሎታል!" ይላሉና፡፡ ኢየሱስ "ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና… አትንኪኝ" አለ፡፡ ኢየሱስ በዚያ ጊዜና ሌሎች እንዲነኩት በፈቀደበት ጊዜ መካከል ወደ እግዚአብሔር አብ አርጎ ራሱን እንደ መሥዋዕት አሳየ፤ እናም ክቡራትና ክቡራን! ኢየሱስ ተመልሶ ባይመጣ ኖሮ፤ ሌሎች እንዲነኩት ባይፈቅድ ኖሮ፤ ያ ማለት መሥዋዕቱ ተቀባይነት አላገኘም ማለት ይሆን ነበር፡፡ ነገር ግን ተመልሶ በመምጣት "ንኩኝ!" ስላለ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፤ ተቀባይነት አግኝቷል!

**21. <u>ምንም አልተደነቀችም</u>**

ማርያም እየሱስን በህይወት ስታየው ምንም መደነቅ አላሳየችም ነበር። ለምን? ተሰቅሎ ሙቶ ነበር ብላ የምታስብ ከሆነ በህይወት ስትመለከው መደነቅ ነበረባት። ነገር ግን ይህንን አስመልክቶ ምንም የተነገረን ነገር የለም። እንዲሁ መደበኛ የቃላት ልውውጥ ማድረጋቸውን ብቻ ነው መጽሀፉ ላይ የምናገኘው። ይህ ደግሞ ለምን የሚል ጥያቄ እንድናነሳ ያስገድደናል።

እስኪ እናንብበው፡-

> *ኢየሱስም፡- አንቺ ሴት፥ ስለ ምን ታለቅሻለሽ? ማንንስ ትፈልጊያለሽ? አላት። እርስዋም የአትክልት ጠባቂ መስሎአት፡- ጌታ ሆይ፥ አንተ ወስደኸው እንደ ሆንህ ወዴት እንዳኖርኸው ንገረኝ እኔም እወስደዋለሁ አለችው። ኢየሱስም፡- ማርያም አላት። እርስዋ ዘወር ብላ በዕብራይስጥ፡- ረቡኒ አለችው፤ ትርጓሜውም፡- መምህር ሆይ ማለት ነው። ኢየሱስም፡- ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ፤ ነገር ግን ወደ ወንድሞቼ ሄደሽ፡- እኔ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ ዓርጋለሁ ብለሽ ንገሪአቸው አላት። መግደላዊት ማርያም መጥታ ጌታን እንዳየች ይህንም እንዳላት ለደቀ መዛሙርቱ ነገረች። (ዮሐንስ 20፡15-18*

የአሕመዲያ ሙስሊሞች ኢየሱስ በመስቀል ላይ ስላልሞተ መግደላዊት ማርያምም በሕይወት እንደምታገኘው እርግጠኛ ስለነበረች አልተደነቀችም ይላሉ፡፡ ሆኖም እነርሱ እንደሚሉት ኢየሱስ መስቀል ላይ አልሞተም ቢባል እንኳ በሕይወትና በሞት መካከል ሆኖ ለሦስት ቀናት የተቀበረ ሰው፣ እንደ ሲሚንቶ የሚያጣብቀውን መቶ ፓውንድ ከርቤና እሬት አራግፎ፣ በመቃብሩ ላይ የተገጠመውን ድንጋይ አንከባሎ፣ ጠባቂ ወታደሮችን አልፎ፣ ጤነኛ ሆኖ በሚስማር በተቸነከሩት እግሮቹ ቆሞ ቢታይ አለመደንገጥ እንዴት ይቻላል? ይህ ክስተት የትንሣኤን ያህል አስደንጋጭ ነው፡፡ ስለዚህ ኢየሱስ ለማርያም የታያት ከሞት ተነስቶ ቢሆንም ባይሆንም መደንገጧ አጠያያቂ አይደለም፡፡ ኢየሱስ ማርያምን በስሟ በጠራት ጊዜ “ረቡኒ” በሚለው ቃሏ ውስጥ የነበረውን የድንጋጤና የግርምት ስሜት ማሰብ አያዳግትም፡፡ ሐዋርያው ዮሐንስ ተደራሲያኑ ሁኔታውን የማገናዘብ በቂ ችሎታ እንዳላቸው ስለሚያውቅ የማርያምን ድንጋጤና ግርምት መዘገብ አላስፈለገውም፡፡

**22. <u>የኢየሱስ መብላት</u>**

ደቀመዛሙርት ወደ ነበሩበት የላይኛው ክፍል ኢየሱስ ሂዶ በነበረበት ወቅት የተከሰተውን ክስተት ወንጌላት እንደሚከተለው ዘግበውት እናገኛለን።

«እነርሱም ከተጠበሰ ዓሣ አንድ ቁራጭ፥ ከማር ወለላም ሰጡት፤ ተቀብሎም በፊታቸው በላ።» ሉቃስ 24፡42-43

«ኢየሱስም፡- ኑ፥ ምሳ ብሉ አላቸው። ከደቀ መዛሙርቱ አንድ ስንኳ፡- አንተ ማን ነህ? ብሎ ሊመረምረው የደፈረ አልነበረም፤ ጌታ መሆኑን አውቀው ነበርና። ኢየሱስም መጣና እንጀራ አንሥቶ ሰጣቸው፥ እንዲሁም ዓሣውን።» ዮሀንስ 21፡12-13

የሰው ልጅ አካሉ እንጅ መንፈስ ከሆነ ምግብና መጠጥ አያስፈልገውም። ኢየሱስ ደግሞ ሙቶ ተነስቷል። ሙቶ የተነሳ አካል በጭራሽ ምግብን ሊመገብ አይችልም። ታዲያ እየስ ሙቶ ከተነሳ እንዴት ምግብ ሊመገብ ቻለ?

ደራሲው ስለ ትንሣኤ አካል ሁለት ሐሰተኛ ነገሮችን ተናግሯል፡፡ የመጀመርያው የትንሣኤ አካል መንፈስ እንደሆነ መናገሩ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ምግብ አለመብላቱን መናገሩ ነው፡፡ የትንሣኤ አካል መንፈሳዊ እንጂ መንፈስ አይደለም፡፡ እስልምናም ሆነ ክርስትና የትንሣኤ አካል መንፈስ እንደሆነ አያስተምሩም፡፡ ከሞት የሚነሳው የሞተው ቁሳዊው አካላችን እንጂ በዕለተ ትንሣኤ መንፈስ ወደ መሆን አንለወጥም፡፡ መንፈስ የመሆን የመሆንማ ነፍሳችን መንፈስ ስለሆነች የሞተው ሥጋችን ከሙታን መነሣት ባላስፈለገው ነበር፡፡ ኢየሱስም የቀደመውን አካሉን መቃብር ውስጥ ትቶ መንፈስ ሆኖ ከመቃብር አልወጣም፡፡ ይልቅ ያንኑ አካል ይዞ በመነሳት እርሱ ራሱ መሆኑንና ከሞት መነሣቱን ምግብን በፊታቸው በመብላት አረጋገጠላቸው፡-

> *"እርሱም፦ ስለ ምን ትደነግጣላችሁ? ስለ ምንስ አሳብ በልባችሁ ይነሣል? እኔ ራሴ እንደ ሆንሁ እጆቼንና እግሮቼን እዩ፤ በእኔ እንደምታዩት፥ መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና እኔን ዳስሳችሁ እዩ አላቸው። ይህንም ብሎ እጆቹንና እግሮቹን አሳያቸው። እነርሱም ከደስታ የተነሣ ገና ስላላመኑ ሲደነቁ ሳሉ፦ በዚህ አንዳች የሚበላ አላችሁን? አላቸው። እነርሱም ከተጠበሰ ዓሣ አንድ ቁራጭ፥ ከማር ወለላም ሰጡት፤ ተቀብሎም በፊታቸው በላ።" (ሉቃስ 24፡38-43)*

የትንሣኤ አካል ልዕለ ተፈጥሯዊ ቢሆንም ነገር ግን ተፈጥሯዊ አካል ማድረግ የሚችላቸውን ነገሮች ማድረግ ይችላል፡፡ በተዘጋ ደጅ ውስጥ አልፎ ይገባል ነገር ግን ይዳሰሳል፤ ምግብ መብላት አያስፈልገውም ነገር ግን መብላት ይችላል፡፡ በገነት ውስጥ ምግብ እንዳለ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (ማርቆስ 14፡25፣ ራዕይ 2፡7፣ 22፡1-3)፡፡ እስልምና ስለ ልቅ ወሲብ በማስተማር ገነትን የዝሙት ቦታ ቢያስመስልም የትንሣኤ አካል ምግብ እንደሚበላና ሌሎች የቁሳዊ አካላት ተግባራትን መፈፀም እንደሚችል ያስተምራል፡፡ እንዲያውም በእስልምና ገነት የገቡ ሰዎች የመጀመርያው ምግብ የዓሣ ጉበት ነው (ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅፅ 4፣ መጽሐፍ 55፣ ሐዲስ 546)፡፡ ታድያ ኢየሱስ በትንሣኤው አካል ሆኖ ዓሣ መብላቱ ለምን ይሆን ጥያቄ የፈጠረበት? ደራሲው ስለ ትንሣኤ አካል ምንነትና ባሕርይ የተናገረው ከክርስትናም ሆነ ከእስልምና አስተምሕሮ ጋር ይጋጫል፡፡ ሃይማኖቱን አያውቅም ወይስ አውቆ እያወናበደ ነው?

23. <u>የዮናስ ኢየሱስ እውን ትንቢቱን አማልቷልን?</u>

አይሁዳዊያን በልምዳቸው ነብያትን የመፈታተን ባህሪ ነበራቸው። በዚህ ባህሪያቸው ምክንያትም ኢየሱስን እንዲሁ ተፈታትነውታል፡፡ በመሆኑም ከሱ ምልክት እንዲያዩ አጥብቀው ሲጠይቁት ማቴዎስ ወንጌል 12፡40 ላይ

*«ለመንዝራ ትውልድ ምልክት ይሻል ከነብዩ ዮናስ በላይ ምልክት የለም ነብዩ ዮናስ በአሳ ነባሪ ሆድ ውስጥ ሶስት ቀንና ለሶስት ሌሊት እንደነበረው የሰው ልጅም በምድር ልብ ውስጥ ለሶስት ቀንና ለሶስት ሌሊት ይኖራል»*

ብሎ ተንብዮአል፡፡ ይህንን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንቢት ከሞት መነሳቱ ጋር በማያያዝ ማቴዎስ ወንጌል 27፡63

*«ጌታ ሆይ ያ አሳች በሕይወት ገና ሳለ ከሶስት ቀን በኃላ እነሳለሁ እንዳለ ትዝ አለን»*

*ሉቃስ 24፡46 «ክርስቶስ መከራ ይቀበላል በሶስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሳል»* ተብሎ ተጽፏል ነገር ግን ዋናው ጥያቄ ትንቢቱ ተፈጽሟል ወይ ነው እስኪ እንመልከት፡-

ትንቢቱ በአጭሩ ሲብራራ ነብዩ ዮናስ በአሳ ነባሪ ሆድ ውስጥ ለሶስት ቀናትና ለሦስት ሌሊቶች በአሳ ነባሪው ሆድ ውስጥ ሳይሞት ህያው ነበር። ከአሳው ነባሪ ሆድ ውስጥም ሲወጣ ህያው ነበር አልሞተም። ያ ማለት ኢየሱስም የሰው ልጅ **ሳይሞት** በምድር ልብ ውስጥ ለሶስት ቀናትና ሌሊቶች ይቆያል ማለት ነው፡፡ ይህ ማለትም ኢየሱስ ክርስቶስ በትንቢቱ መሰረት አልሞተም ነበር ማለት ነው።

ደራሲው ኢየሱስ ያልተናገረውን ሐሳብ ወደ ክፍሉ ጨምሯል፡፡ ኢየሱስ እንደ ዮናስ ሕያው ወይም ሙት እንደሚሆን አልተናገረም፡፡ ንፅፅሩ ከሦስት ቀናት ጋር ነው፡፡ ዋናው ነጥብ የጊዜው ርዝማኔ ስለመሆኑ "ሦስት" የሚለው ቃል አራት ጊዜ ተደጋግሞ መጠቀሱ አንዱ ማረጋገጫ ነው፡-

> *"… ዮናስ በዓሣ አንባሪ ሆድ <u>ሦስት</u> ቀንና <u>ሦስት</u> ሌሊት እንደ ነበረ፥ እንዲሁ የሰው ልጅ በምድር ልብ <u>ሦስት</u> ቀንና <u>ሦስት</u> ሌሊት ይኖራል። የነነዌ ሰዎች በፍርድ ቀን ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥተው ይፈርዱበታል፤ በዮናስ ስብከት ንስሐ ገብተዋልና፥ እነሆም፥ ከዮናስ የሚበልጥ ከዚህ አለ።" (ማቴዎስ 12፡40)*

ኢየሱስ ታሪካዊ ክርስተቶችን ለገዛ ሕይወቱ እንደ ምሳሌ ሲጠቅስ ይህ የመጀመርያው ጊዜ አይደለም፡፡ ለምሳሌ ያህል በመስቀል ላይ መሰቀሉን በተመለከተ እንዲህ ብሎ ነበር፡-

> *"ሙሴም በምድረ በዳ እባብን እንደ ሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ይገባዋል።" (ዮሐንስ 3፡14-15)*

የደራሲውን አካሄድ ከተጠቀምን አንድ ሰው ከዚህ ምሳሌ በመነሳት "የነሃሱ እባብ ሕይወት ስላልነበረው ኢየሱስም ሲሰቀል ሕያው አልነበረም" ሊል ይችላል፡፡ ነገር ግን የንፅፅሩ ነጥብ መሰቀል እንጂ ሕያው መሆን አለመሆን አይደለም፡፡ ልክ እንደዚሁ የዮናስ ምሳሌ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት የመቆየት ጉዳይ እንጂ ሕያው ስለመሆን ስላለመሆን አይደለም፡፡ ኢየሱስ

ለደቀ መዛሙርቱ እንደሚሰቀልና እንደሚሞት በተደጋጋሚ ነግሯቸው ሳለ ይህንን ምሳሌ ሕያው ሆኖ እንደሚቀበር የተናገረ በማስመሰል መተርጎም ስሜት አይሰጥም (ማቴዎስ 16:21-23፣ 17:9፣ 22-23፣ 20:17-19፣ 21:33-40)፡፡

24. <u>የደቀመዛሙርቱ ጸሎት</u>

ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ሳይቀር ልዩ ለሆነ ጸሎት ያነሳሳቸው ነበር። ይህ ጸሎትም እዛው ቦታ ላይ እሱ እንደጸለየው ከሞት ሊያድነው ወደሚችል አካል ያንን ህልም ይዞ ነበር የቀረበው።

«በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ከእነርሱ ጋር ጌቴሴማኒ ወደምትባል ስፍራ መጣ ደቀ መዛሙርቱንም፡- ወዲያ ሄጄ ስጸልይ ሳለ በዚህ ተቀመጡ አላቸው። ጴጥሮስንም ሁለቱንም የዘብዴዎስን ልጆች ወስዶ ሊያዝን ሊተከዝም ጀመር። ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ እጅግ አዘነች፤ በዚህ ቆዩ ከእኔም ጋር ትጉ አላቸው። ጥቂትም ወደ ፊት እልፍ ብሎ በፊቱ ወደቀና ሲጸልይ፡- አባቴ፥ ቢቻልስ፥ ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ፤ ነገር ግን አንተ እንደምትወድ ይሁን እንጂ እኔ እንደምወድ አይሁን አለ። ወደ ደቀ መዛሙርቱም መጣ፤ ተኝተውም አገኛቸውና ጴጥሮስን፡- እንዲሁም ከእኔ ጋር አንዲት ሰዓት እንኳ ልትተጉ አልቻላችሁምን? ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ፤ መንፈስስ ተዘጋጅታለች ሥጋ ግን ደካማ ነው አለው።» ማቴዎስ 26:36-41

የኢየሱስ ስቅለት ከጸሎቱ አንፃር ስላለው አንድምታ ቀደም ሲል ተጠይቆ መልስ ሰጥተናል፡፡

25. <u>የኢየሱስ ሲጋና አጥንት</u>

ኢየሱስ ወደ ደቀመዛሙርቱ መጥቶ በነበረበት ወቅት እጆቹንና እግሮቹን እያሳየ ህያው መሆኑን ሊያረጋግጥላቸው ሞክሯል። የሞተ አካል መንፈስ እንደሆነ መንፈስ ደግሞ ስጋና አጥንት እንደሌለው እርሱ ግን ስጋና አጥንት ስላለው አለመሞቱን በተዘዋዋሪ እያረጋገጠላቸው ነበር።

«ነገር ግን ደነገጡና ፈሩ መንፈስም ያዩ መሰላቸው። እርሱም፡- ስለ ምን ትደነግጣላችሁ? ስለ ምንስ አሳብ በልባችሁ ይነሣል? እኔ ራሴ እንደ ሆንሁ እጆቼንና እግሮቼን እዩ፤ በእኔ እንደምታዩት፥ መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና እኔን ዳስሳችሁ እዩ አላቸው። ይህንም ብሎ እጆቹንና እግሮቹን አሳያቸው።» ሉቃስ 24:37-40

ሞቶ በአጸደ ነፍስ ያለ ሰው በመንፈስ ዓለም ይኖራል፡፡ ነገር ግን ሞቶ ከሙታን የተነሳ ሰው የሰው አካል አለው፡፡ ስለዚህ ኢየሱስ እያረጋገጠላቸው የነበረው ከሞት መነሳቱን እንጂ አለመሞቱን አይደለም፡፡ ከእርሱ በማስከተል ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፡-

*"እርሱም፡- ከእናንተ ጋር ሳለሁ በሙሴ ሕግና በነቢያት በመዝሙራትም ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይገባል ብዬ የነገርኋችሁ ቃሌ ይህ ነው አላቸው። በዚያን ጊዜም መጻሕፍትን ያስተውሉ ዘንድ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው፤ <u>እንዲህም አላቸው፡- ክርስቶስ መከራ ይቀበላል</u> **<u>በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሣል</u>**፥ በስሙም*

*ንስሐና የኃጢአት ስርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል ተብሎ እንዲሁ ተጽፎአል። እናንተም ለዚህ ምስክሮች ናችሁ።" (ሉቃስ 24፡44-48)*

ደራሲው ይህንን ጥቅስ ቆርጦ ያስቀረው ለምን ይሆን?

**26. <u>የኢየሱስ ቁስል</u>**

ኢየሱስ ቁስሉን ማሳየቱ ያለመሞቱ ትልቅ ማስረጃ ነው። ለደቀመዛሙርቱ አካላቱን በማሳየት እንዳሰቡት እንዳልሞተና መጀመሪያውም የሚያውቁት አካል አብሮት እንዳለ እያብራራላቸው ነበር።

*«ሌሎቹም ደቀ መዛሙርቱ፡- ጌታን አይተነዋል አሉት። እርሱ ግን፡- የችንካሩን ምልክት በእጆቹ ካላየሁ ጣቴንም በችንካሩ ምልክት ካላገባሁ እጄንም በጎኑ ካላገባሁ አላምንም አላቸው። ከስምንት ቀን በኋላም ደቀ መዛሙርቱ ደግመው በውስጥ ነበሩ፥ ቶማስም ከእነርሱ ጋር ነበረ። ደጆች ተዘግተው ሳሉ ኢየሱስ መጣ፤ በመካከላቸውም ቆሞ፡- ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው። ከዚያም በኋላ ቶማስን፡- ጣትህን ወደዚህ አምጣና እጆቼን እይ፤ እጅህንም አምጣና በጎኔ አግባው፤ ያመንህ እንጂ ያላመንህ አትሁን አለው።»ዮሀንስ 20፡25-27*

አሁንም ጠያቂው ከሞት የተነሳ ሰው መንፈስ ይሆናል የሚለውን በክርስትናም ሆነ በእስልምና ድጋፍ የሌለውን ስሁት አመለካከት እያስተጋባ ነው፡፡ ኢየሱስ ከሞት የተነሳው በቀደመው አካሉ ነው፡፡ ይህ አካል ደግሞ ለኛ ሲል ያስተናገደውን የመከራ ምልክቶች ይዟል፡፡ የችንካሩ ምልክት ተዓምራዊ በሆነ መንገድ አልጠፋም፡፡ እንዲያ ቢሆን ኖሮ ደቀ መዛሙርቱ እርሱ መሆኑን በተጠራጠሩ ነበር፡፡ ቶማስ የተወጋውን እጁንና ጎኑን እንደ ማስረጃ መቁጠሩ ለዚህ ጥሩ ማሳያ ነው፡፡

**27. <u>ለእየሱስ ፈተና</u>**

የኢየሱስ ስቅለት አይሁዳውያን አስቀምጠውት ለነበረው መስፈርት ማጠናከሪያ ከመሆን የዘለለ ብዙ ፋይዳ አልነበረውም። በስቅለቱ ወቅት አይሁዶች እንዲህ ይሉ ነበር፡-

*"ቤተ መቅደስን የምታፈርስ በሦስት ቀንም የምትሠራው፥ ራስህን አድን፤ የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንህ ከመስቀል ውረድ አሉት።" (ማቴ 27: 40)*

*"ሌሎችን አዳነ፥ ራሱን ሊያድን አይችልም፤ የእስራኤል ንጉሥ ከሆነ፥ አሁን ከመስቀል ይውረድ እኛም እናምንበታለን።" (ማቴ 27: 42)*

የሚያሳዝነው አይሁዶች ትክክል ነበሩ..!

የእግዚአብሔር ዓላማ መሲሁ ሞቶ የዓለምን ሕዝብ ከኃጢአት ያድን ዘንድ ሆኖ ሳለ አይሁድ ተፃራሪውን ማመናቸው ትክክል እንዲሆኑ የሚያደርጋቸው በምን ስሌት ነው? ኢየሱስ ከዚያ ቀደም ብዙ ምልክቶችን በማሳየት መሲህ መሆኑን አረጋግጦላቸዋል እኮ! አሁን ደግሞ የእግዚአብሔርን ዓላማ እየፈፀመ በነበረበት ሰዓት ልበ ደንዳና አይሁድን ለማሳመን ሲል የእግዚአብሔርን ዓላማ ማክሸፍ ነበረበት? አይሁድ ብዙ ነቢያትን እንደገደሉ ይታወቃል፡፡ ሲገድሉ ደግሞ

እውነተኛነታቸውን ባለመቀበል ነበር፡፡ ስለዚህ መሲሁን ሲገድሉት ትክክል የሚሆኑት እንዴት ነው? ኅበዝ እያሰብን እንጠይ እንጂ!

ሌላው ኢየሱስ ስለ መቅደሱ መፍረስና በሦስተኛው ቀን መሠራት ሲናገር ስለ ሞትና ስለ ትንሣኤው እየተናገረ እንደነበር ደራሲው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልፅ የተጻፈውን አለማወቁ ይገርማል፡-

> *"ኢየሱስም መልሶ፡- <u>ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፥ በሦስት ቀንም አነሣዋለሁ አላቸው።</u> ስለዚህ አይሁድ፡- ይህ ቤተ መቅደስ ከአርባ ስድስት ዓመት ጀምሮ ይሠራ ነበር፥ አንተስ በሦስት ቀን ታነሣዋለህን? አሉት። <u>እርሱ ግን **ስለ ሰውነቱ ቤተ መቅደስ ይል** ነበር</u>። ስለዚህ **<u>ከሙታን ከተነሣ በኋላ</u>** <u>ደቀ መዛሙርቱ ይህን እንደ ተናገረ አሰቡና መጽሐፍንና ኢየሱስ የተናገረውን ቃል አመኑ።"</u> (ዮሐንስ 2፡19-22)*

ኢየሱስ ሞቶ በመነሳት የእግዚአብሔርን ዓላማ አሳክቷል፤ የአይሁድንም የተሳሳተ እሳቤ አክሽፏል፡፡

**28. <u>ራስን ማዳን</u>**

ኢየሱስ ራሱን ማዳን ይችላል? አምላክ ከሆነ ራሱን ማዳን አይከብደውም። አምላክ በተራ ፍጡራኖቹ ተይዞ ተገርፎና ተሰቃይቶ የሚገደል አካል አይደለም። ራሱን ማዳን ካልቻለና ተዋርዶ የፍጡራኑን ፍርድ በተሸናፊነት ከተቀበለ ግን እርሱ አምላክ አይደለም ማለት ነው።

ኢየሱስ ስለ እኛ ቤዛ ለመሆን ወዶና ፈቅዶ ሰው ሆኖ ወደ ዓለም መጥቷል፡፡ የሞተው ራሱን ማዳን ስለማይችል ሳይሆን መሞት ስለፈለገ ነው፡፡ የሞተልን ደግሞ በማይሞተው መለኮታዊ ባሕርዩ ሳይሆን መሞት በሚችለው ሰብዓዊ ባሕርዩ ነው፡፡ ይህ የኢየሱስን አምላክነትም ሆነ ቤዛነት ለማስተባበል የሚበቃ ሙግት አይደለም፡፡

**29. <u>ኢየሱስ ስቀሉኝ አላለም</u>**

በመጨረሻ ወቅት ላይ ሳይቀር ኢየሱስ የመሠቀል ፍላጎት አልነበረውም። በዛ ቀውጢ ወቅት እንኳን "ይሰቀል" ሲሉ የነበሩት አይሁዳውያን እንጅ እርሱ አልነበረም።

*" ጲላጦስ፡- ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን እንግዲህ ምን ላድርገው? አላቸው፤ ሁሉም፡- ይሰቀል አሉ።"*

*(ማቴ 27: 22)*

የኢየሱስ የመምጣት አላማው መሠቀልና በዛ ምክንያት የሰው ልጅን ማዳን ከነበረ እንዴት አንድ ጊዜ እንኳን ይህን አስመልክቶ እንዲሰቅሉትና ተልዕኮውን መጨረስ እንደሚፈልግ ፍቃደኝነቱን አልገለፀም? በተቃራኒው እንዳይሞት ሲታገል እንጅ ወደ ስቅለቱ በፍቃዱ ሲገባ አንድም ጊዜ አናስተውልም።

ኢየሱስ መሞቱ ላይቀር “ስቀሉኝ” ምን አስባለው? አስፈላጊ አልነበረም፡፡ ነገር ግን እያንዳንዱ እርምጃው ወደ መስቀል የሚወስድ ነበር፡፡ አይሁድ እንደሚሰቅሉት እያወቀ ነበር ወደ ኢየሩሳሌም የሄደው፡፡ እንደሚሰቀል አውቆ ከሐዋርያቱ ጋር የመጨረሻውን እራት በላ፡፡ በእራቱ ወቅት የአስቆሮቱ ይሁዳን “የምታደርገውን ቶሎ ብለህ አድርግ” በማለት አሳልፎ እንደሚሰጠው ማወቁን ነግሮታል (ዮሐንስ 13፡27)፡፡ ከእራት በኋላ በቀጥታ የሄደው ከሐዋርያቱ ጋር ቀደም ሲል ወደሚሰበሰቡበት ቦታ ነበር፤ የአስቆሮቱ ይሁዳ ያንን ቦታ እንደሚያውቅና መርቶ እንደሚያመጣቸው ያውቃል፤ ሰዋራ ቦታ መምረጥ ሲችል ይሁዳ የሚያውቀውን ቦታ መረጠ (ዮሐንስ 18፡2)፡፡ የመስቀሉን መከራ በማሰብ በጭንቀት ሆኖ ቢጸልይም በመጨረሻዋ ሰዓት ግን በፈቃዱ ራሱን አሳልፎ ሰጥቷል (ዮሐንስ 18፡5-8)፡፡ ሲፈርዱበትም በዝምታ ታገሰ እንጂ ከፍርድ ራሱን ነፃ ለማውጣት ስለ መብቱ አልተከራከረም (ኢሳይያስ 53፡7፣ ማቴዎስ 27፡12)፡፡ እንደሚሰቀል ለሐዋርያቱ ደጋግሞ ነግሯቸዋል፡፡ እንዳይሰቀል ስለመከረው ደግሞ ጴጥሮስን መረር ባለ ሁኔታ ገስፆታል፤ ይህም ቆራጥነቱን ያሳያል፡-

> *“የሰው ልጅ ብዙ መከራ ሊቀበል፥ ከሽማግሌዎችም ከካህናት አለቆችም ከጻፎችም ሊጣል፥ ሊገደልም ከሦስት ቀንም በኋላ ሊነሣ እንዲገባው ያስተምራቸው ጀመር፤ ቃሉንም ገልጦ ይናገር ነበር። ጴጥሮስም ወደ እርሱ ወስዶ ይገሥጸው ጀመር። እርሱ ግን ዘወር አለ ደቀ መዛሙርቱንም አይቶ ጴጥሮስን ገሠጸውና፦ ወደ ኋላዬ ሂድ፥ አንተ ሰይጣን፤ የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን ነገር አታስብምና አለው።” (ማርቆስ 8፡31-33)፡፡*

ይህ ሁሉ ማስረጃ ባለበት ሁኔታ ኢየሱስ ለመሰቀል ፈቃደኝነቱን አልገለፀም እንዴት ሊባል ይችላል?

**30. ደስተኛ አልነበረም**

ኢየሱስ ወደ መስቀል የሄደው ደስተኛ ሁኖ አልነበረም። በውሳኔው አዝኖና በተስፋ መቁሰጥ ውስጥ ሁኖ እንደነበር ከንግግሩ እንረዳለን

*" ኢየሱስም መልሶ፦ መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም፤ መንግሥቴስ ከዚህ ዓለም ብትሆን፥ ወደ አይሁድ እንዳልሰጥ ሎሌዎቼ ይዋጉልኝ ነበር፤ አሁን ግን መንግሥቴ ከዚህ አይደለችም አለው።"*

*(ዮሐ 18: 36)*

ኢየሱስ በዛ ወቅት ምንም ማድረግ እንዳልቻለ ከአንቀፁ እንረዳለን። ይህን ለሰው ልጆች አዲስ'ምዕራፍ የሚከፍት ክስተት በተስፋ መቁረጥ ውስጥ እንደተፈጸመ ማሰብ ስሜት ይሰጣልን? የነፃነት ታጋዬች እንኳን ተይዘው ሲቀጡ በኩራት አንገታቸውን ቀና አድርገው በደስተኛ ስሜት ውስጥ ሆነው ሲሞቱ በታሪክ አይተናል። ታዲያ ለአለም ሀጥያት የሚሰቀለው ኢየሱስ ከእነሱ ያንሳልን? እነሱ ለተነሱለት አላማ ለመሞት ደፋሮች ሆነው እርሱ ለአለም ሀጥያት ለመሞት አዘነ መባልስ ያሳምናል?

አንደኛ፡- ኢየሱስ ሥቃዩን አስቦ ተጨንቋል፣ አዝኗል፤ ነገር ግን ለሰው ልጆች በሚከፍለው ዋጋ በፀፀት ስሜት ተሞልቶ አላዘነም፤ ተስፋም አልቆረጠም፡፡ ሁለቱ ኀዘኖች ለየቅል ናቸው፡፡ ለምሳሌ ያህል አንዲት እናት ለልጇ ኩላሊቷን መስጠት ቢኖርባት የአካል ክፍሏ በመጉደሉና የህመም ስሜት በማስተናገዷ ምክንያት ልትጨነቅና ልታዝን ትችላለች፤ ነገር ግን ዋናው

ነጥብ ልጇ መትረፉ ሲሆን ለልጇ ያላት ፍቅር ጭንቀቷንና ኀዘኗን እንድታሸንፍ ምክንያት ይሆናታል፡፡ ስለዚህ ስላዘነችና ስለተጨነቀች የዚህችን እናት ፍቅር የሚጠራጠር አይኖርም፡፡

ሁለተኛ፡- ኢየሱስ የተሰማውን ትክክለኛ ስሜት ደብቆ ሐሰተኛ ጅጋኔ (False Bravado) ያሳይ ዘንድ እንደ ሰው ልጆች ግብዝ አይደለም፡፡ እንደው ማን ይሙት አሣቃቂ በሆነ ሁኔታ ለመሞት እየተወሰደ ሳለ የደስታና የእፎይታ ስሜት የሚሰማው ማን ነው? ሐሰት! የሰው ልጆችን ኃጢአት በሙሉ ጨምሮ ክርስቶስ ከተሸከመው መከራ ጋር የሚመጣጠን መከራ ተሸክሞስ በደስተኛ ስሜት ውስጥ ሆኖ ሞቷል ተብሎ በምሳሌነት ሊጠቀስ የሚችል ማን አለ? የክርስቶስን ጭንቀት ይበልጥ ለመረዳት ለአሕመዲን ጀበል ከተሰጠ ምላሽ የተወሰደውን ተከታዩን ሐሳብ ማንበብ ጠቃሚ ነው፡-

> ኢየሱስ ከፊቱ ያለውን መከራ በዝርዝር ያውቅ ስለነበር ተጨንቋል ነገር ግን ቀደም ሲል እንደተመከለትነው በፈቃዱ ራሱን አሳልፎ ሰጠ እንጂ አልሸሸም፡፡ ጠያቂው የመስቀል መከራ ለምን ይኾን እንዲህ የቀለለባቸው? ምናልባት ስለ ስቅለት ዝርዝር ሂደት መረጃ ስለሌላቸው ይሆናል፡፡
>
> አንድ ሰው ከመሰቀሉ በፊት በከባድ ኹኔታ ይገረፋል፡፡ ኢየሱስ በሮማውያን እጅ ብቻ ሳይኾን በአይሁድ ሸንጎም ተገርፏል፡፡ አይሁድ 40 ጅራፍ ነው የሚገርፉት፡፡ ከ40 አልፈው ህጉን እንዳይተላለፉ ምናልባት የቆጠራ ስህተት ካለ በሚል 39 ላይ ያቆማሉ፡፡ ሮማውያን ደግሞ የፈለጉትን ያህል ነው የሚገርፉት፡፡ አለንጋዎቹ ብዙ ቅርንጫፎች ያሏቸው ሲሆኑ በየአንጓዎቹ ላይ የብረትና የአጥንት ጉጠቶች ይሰካሉ፡፡ ጅራፎቹ በተገራፊው ጀርባ ላይ ሲያርፉ ብረቶቹና አጥንቶቹ ቆዳውንና ሥጋውን ቦጭቀው ያነሳሉ፡፡ ከጥቂት ጅራፎች በኋላ የሰለባው የላይኛው ቆዳ ተገፎ ከስር ያለው ጡንቻ ይከፈታል፡፡ ግርፋቱ ሲቀጥል ጡንቻዎቹ ተበጣጥሰው የደም ስሮች መቆራረጥ ይጀምራሉ፤ ከተቆራረጡት ስሮች ውስጥ ደም ይንዶለዶላል፡፡ ብዙ ጊዜም የተገራፊዎቹ ሆድ ተከፍቶ አንጀታቸው እስከመውጣት ይደርሳል፡፡ ከዚህ የተነሳ ብዙዎቹ እዚያው ይሞቱ ነበር፡፡ ይህ ከሆነ በኋላ ወደ መሰቀያ ቦታ ተወስደው እጆቻቸውና እግሮቻቸው ሰባት ኢንች በሚረዝሙ ሚስማሮች በእንጨት ላይ ይቸነከራሉ፡፡ የእጅ መዳፎች የአንድን ሰው ክብደት መሸከም ስለማይችሉ ሚስማሮቹ ከመዳፍ ከፍ ብለው በክንድ አጥንቶች መካከል ይመታሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ሚስማሮቹ የእጅ ነርቮችን በጣጥሰው ስለሚያልፉ ሰለባዎቹ ለከፍተኛ የሥቃይ ስሜት ይዳረጋሉ፡፡ ወደ ላይ ቀጥ ተደርገው ስለሚሰቀሉ መተንፈስ በእጅጉ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ ተወጥረው ከተሰቀሉ ወዲያውኑ ታፍነው ስለሚሞቱ እግሮቻቸው ትንሽ አጠፍ ተደርገው ይቸነከራሉ፡፡ ለመተንፈስ በእግሮቻቸው ላይ በተሰካው ሚስማር ላይ ቆመው ወደ ላይና ወደ ታች እንደ ፓምፕ መንቀሳቀስ ያስፈልጋቸዋል፡፡ አየር ለማስገባት እግሮቻቸውን አጥፈው ወደ ታች ዝቅ ይላሉ፡፡ ለማስወጣት ደግሞ እግሮቻቸውን ወጥረው ወደ ላይ ይላሉ፡፡ በዚህ ጊዜ የተሰቀሉበት ደረቅ እንጨት በግርፋት የቆሰለውን ጀርባቸውን ይፈቀፍቃቸዋል፡፡ እንቅስቃሴውን ለአፍታ ካቆሙ ወዲያውኑ ታፍነው ይሞታሉ፡፡ ለዚህ ነው ከኢየሱስ ጋር የተሰቀሉትን ወንበዴዎች ቶሎ እንዲሞቱ ለማድረግ ጭኖቻቸውን የሰበሩት፡፡ (Nabil Qureshi: *Seeking Allah, Finding Jesus*; Zondervan, Grand Rapids, Michigan 2014, pp. 150-151)
>
> ይህንን ሥቃይ ለማስታገስ ሮማውያን ብዙ ጊዜ ሀሞት፣ ከርቤና የወይን ጠጅ የተቀላቀለበትን አደንዛዥ መጠጥ ይሰጧቸው ነበር፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ግን ይህንን መጠጥ በመጠጣት ህመሙን ከማስታገስ ይልቅ ሙሉ ሥቃዩን በመቀበል መሞትን መረጠ (ማርቆስ 15፡23፣ ማቴዎስ 27፡34)፡፡ የእግዚአብሔር ልጅ ለሦስት ሰዓታት ያህል

በእንዲህ ዓይነት ሥቃይ ውስጥ በማለፍ ነበር የመጨረሻ እስትንፋሱን የተነፈሰው፡፡ የዓለምን ኹሉ ኃጢአት መሸከም ደግሞ ምን ያህል ለሥቃይ እንደሚዳርግ ከእርሱ በስተቀር ማን አየው? እንግዲህ ጠያቂው እንዲህ ዓይነቱን መከራ እንደሚያስተናግድ በማወቁ ምክንያት ኢየሱስ መጨነቁ ተገቢ አልነበረም የሚል የሞኝ ሙግት ነው የገጠሙት!

31. <u>መዳን ለአይሁድ ነው</u>

ኢየሱስ ሲናገር:-

*"እናንተስ ለማታውቁት ትሰግዳላችሁ፤ እኛ መዳን ከአይሁድ ነውና ለምናውቀው እንሰግዳለን።" (ዮሐ 4: 22)*

**ኢየሱስ ይህን ሲናገር ምን ማለቱ ነበር? በስቅለቱ ከነአካቴው የማያምኑት ብሎም እንዲገደል ያደረጉት አይሁዶች ጋ መዳን እንዳለ ይናገራል። ታዲያ መዳን በስቅለት እንደሆነ ያስተማሩት አካላት ይህን የኢየሱስ ንግግር የት ጥለውት ነው?**

ኢየሱስ መዳን “ከአይሁድ ነው” አለ እንጂ “ለአይሁድ ነው” አላለም፡፡ በእርግጥ መዳን ለአይሁድና ለዓለም ሁሉ ነው፡፡ ይህ ማለት ግን በክርስቶስ ያላመኑት አይሁድና የዓለም ሕዝቦች ሁሉ ይድናሉ ማለት አይደለም፡፡ ካመኑ ግን የመዳን ዕድል ለሁሉም እኩል ቀርቧል፡፡ በተጠቀሰው ጥቅስ ውስጥ ጌታ ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ከአይሁድ ዘንድ ለዓለም መዳን እንደሚመጣ ነው፡፡ እርሱም በራሱ በኢየሱስ ተፈፅሟል፡፡ ጌታ ኢየሱስም ሆነ የምሥራቹን እስከ ምድር ዳርቻ የወሰዱት ሐዋርያቱ አይሁዳውያን ነበሩ፡፡ ስለዚህ መዳን ከአይሁድ ነው፡፡ ይህ ምንም ግራ የሚያጋባ ነገር የለውም፡፡

32. <u>ስቅለት ግድያ ነው</u>

ስቅለትን አስመልክቶ ኢየሱስ ይመለከተው የነበረው እንደ ግድያ ተግባር እንጅ መዳንን እንደሚያመጣ ቅዱስ መስዋዕትነት አድርጎ አልነበረም።

*" ሙሴ ሕግን አልሰጣችሁምን? ከእናንተ ግን ሕግን የሚያደርግ አንድ ስንኳ የለም። ልትገድሉኝ ስለ ምን ትፈልጋላችሁ?"*

*(ዮሐ 7: 19)*

*" ነገር ግን አሁን ከእግዚአብሔር የሰማሁትን እውነት የነገርኋችሁን ሰው ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ፤ አብርሃም እንዲህ አላደረገም።"*

*(ዮሐ 8: 40)*

*"ከዚያም ወጥተው በገሊላ በኩል አለፉ፤ ደቀ መዛሙርቱንም ያስተምር ስለ ነበር ማንም ያውቅ ዘንድ አልወደደም፤ ለእነርሱም:- የሰው ልጅ በሰዎች እጅ አልፎ ይሰጣል፥ ይገድሉትማል፥ ተገድሎም በሦስተኛው ቀን ይነሣል ይላቸው ነበር።" (ማር 9: 30-31)*

**ኢየሱስ ስቅለትን እንደመስዋዕትነት ቢያየው ኑሮ ለዚህ ተግባር የሚራሯጡ ሰዎችን በገዳይነት ፈርጆ ደጋግሞ ባልወቀሳቸው ነበር። ለእየሱስ የእርሱ ስቅላት ግድያ እንጅ ሌላ አልነበረም።**

ስቅለት በክፉ ሐሳብ ተነሳስተው ኢየሱስን ከገደሉት ከሮማውያንና ከአይሁድ አኳያ ግድያ ነው፤ ከእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ አኳያ ግን መሥዋዕትነት ነው፡፡ አይሁድና ሮማውያን የልብ ሐሳባቸው ክፉ ስለነበር ተግባራቸው ክፉና ኢ-ፍትሃዊ ነው፡፡ የአንድ ሰው ሞት ለአንዱ ወገን ለነፃነት የተከፈለ መሥዋዕትነት ተደርጎ ሲቆጠር ለሌላው ወገን ደግሞ የአመፅ ቅጣት ተደርጎ ሊታሰብ ይችላል፡፡ ይህንን የሚወስነው የቆምንበት ቦታና ዕይታችን ነው፡፡ ኢየሱስ ወደ ምድር የመጣው ደሙን በማፍሰስ ሕዝቡን ለመቤዠት መሆኑን በተደጋጋሚ ተናግሯል፤ ስለዚህ ስቅለት ለእርሱ መሥዋዕትነት አለመሆኑን መናገር ትልቅ ቅጥፈት ነው፡፡ ኢየሱስ ሊገድሉት የሚፈልጉትን አይሁድ የወቀሳቸው በክፉና ኢ-ፍትሃዊ አስተሳሰባቸው ምክንያት ነው፡፡ ኢየሱስን ለመግደል ይፈልጉ የነበሩት ዓለምን ለማዳን በበጎ ሐሳብ ሳይሆን እርሱን ለማጥፋት በክፉ ሐሳብ በመሆኑ ወቀሳው ትክክል ነው፡፡

## 33. <u>የኢየሱስ ቅሬታ</u>

ኢየሱስ በተሰቀለበት ወቅት እንዲህ ማለቱ ተዘግቧል፡-

*" በዘጠኝ ሰዓትም ኢየሱስ፡- ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ? ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ። ይህም፡- አምላኬ አምላኬ፥ ስለ ምን ተውኸኝ? ማለት ነው።"*

*(ማቴ 27: 46)*

ይህንን አንቀፅ አስመልክቶ ሁለት ጥያቄዎችን ማንሳት እንችላለን።

፩- የመጀመሪያው ጥያቄ ኢየሱስ ለምን ተውኸኝ ሲል ምን ማለቱ ነበር? አምላክ እንደማይተወው ቃል ገብቶለት ነበር? እንደማይተወው ቃል ከገባለት ደግሞ በጠላት እጅ አሳልፎ ሰጥቶ እንደማያስገድለው እየሱስ ያስብ ነበር ማለት ነው። ምክንያቱም እየሱስ ምድር ላይ በነበረበት ወቅት አባቱን ለምኖ ያልተሳካለት ጊዜ አልነበረም። እንዴውም አልአዛርን ከሞት ባስነሳበት ወቅት እንዲህ ብሎ ነበር፡-

*"ድንጋዩንም አነሡት፡- ኢየሱስም ዓይኖቹን ወደ ላይ አንሥቶ፡- አባት ሆይ፥ ስለ ሰማኸኝ አመሰግንሃለሁ። ሁልጊዜም እንድትሰማኝ አወቅሁ ...."*

*(ዮሐ 11:41-42)*

በዚህ እሳቤ ውስጥ ሁኖ ነበር ኢየሱስ ከላይ እንዳየነው እንዳይሰቀል ይለምን የነበረው ነገር ግን አምላክ ቃሉን አልጠበቀለትም። ተወው፤ አሳልፎም ሰጠው። እየሱስም "ለምን ተውኸኝ?" ብሎ በመጨረሻ ሰአት ወቀሳውን አቀረበ

፪- እንደ ክርስትናው አመለካከት ኢየሱስ ለአባቱ ተወዳጅ ልጅ ነው። መፅሀፍ ቅዱስም በግልፅ ሰማያት ተከፍተው ኢየሱስን "የምወደው ልጄ" እንዳለው ይነግረናል። ታዲያ ይህን የሚወደው ልጁን ፀሎት ባለመቀበል ለጠላት አሳልፎ ከሰጠው ለኔና ለአንተ ቃሉን የሚጠብቅ አዛኝ አምላክ ነው ብለን እንዴት ማሰብ እንችላለን? የሚወደው ልጁን ከጠላት ማዳን ያልወደደ አምላክ በምን መስፈርት እኔና አንተን ያድነናል?

ኢየሱስ “አምላኬ አምላኬ ስለምን ተውከኝ” ሲል በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ ስለ እርሱ የተተነበየውን ትንቢት ለመጠቆም የመጀመርያውን ስንኝ እየጠቀሰ ነበር፡፡ በዚያ ቦታ የተከናወኑት ነገሮች ኹሉ እርሱ በጠቀሰው መዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 22 ውስጥ በዝርዝር የተተነበዩ ሲሆን ዳዊት በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ በጸለየው በዚያ ጸሎት ውስጥ የክርስቶስን መከራ የተመለከቱ ብዙ ዝርዝር ጉዳዮች ተተንብየዋል፡፡ በዚያ የቆሙት ሰዎች ያላገጡበት እንደነበር (ሉቃ. 23፡35)፣ ልብሶቹን መከፋፈላቸውን (ዮሐ. 19፡23)፣ በእጀ ጠባቡ ላይ ዕጣ መጣጣላቸውን (ዮሐ. 19፡24)፣ ወዘተ. ከኹሉ በላይ ደግሞ ሰዎችን በመስቀል ላይ ቸንክሮ መግደል ባልተጀመረበት በዳዊት ዘመን እጆቹና እግሮቹ ስለመቸንከራቸው የተነገረው ትንቢት በእጅጉ አስደናቂ ነው (ቁ. 16)፡፡ ስለዚህ ክርስቶስ ጌታችን በመስቀል ላይ ኾኖ የመጀመርያውን ስንኝ መናገሩ ትንቢቱ የተነገረበትን ክፍል ለማመልከት እንጂ ለመጸለይ አልነበረም፡፡

ጠያቂው መጨረሻ ላይ የተናገረው አግራሞትን ያጭራል፡፡ እግዚአብሔር አብ የሚወደውን ልጁን ከመስቀል ስላላዳነው ልንተማመንበት አንችልም ከተባለ ብዙ ቅዱሳን ሰዎችና ነቢያ በጠላቶቻቸው እጅ በግፍ ሲገደሉ ዝምታን መምረጡ በማዳኑ ላይ ጥርጣሬ እንዲገባን ያደርጋል ማለት ነው? በዘመናት መካከል እግዚአብሔር አገልጋዮቹን ከግፈኞች እጅ አድኗል፤ በዚያው ልክ ደግሞ ከዘላለማዊ ፈቃዱና ዕውቀቱ አኳያ ልንረዳቸው የሚገቡ የዝምታ ጊዜያትም ነበሩ፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ክርስቲያኖችም ሆኑ ሙስሊሞች ልዩነት ያላቸው አይመስለኝም፡፡

**34. <u>ስቀለት እርግማን ነው</u>**

በአይሁዳውያን ህግ መሠረት ስቅለት የእርግማን ምልክት ነው።

*" በእንጨት ላይ የተሰቀለ በእግዚአብሔር ዘንድ የተረገመ ነውና ሬሳው በእንጨት ላይ አይደር፤ ነገር ግን አምላክህ እግዚአብሔር ርስት አድርጎ የሰጠህን ምድር እንዳታረክስ በእርግጥ በዚያው ቀን ቅበረው።"*

*(ዘዳግም 21: 23)*

በዚህም መሠረት ኢየሱስ ተሰቅሏል ካልን የተረገመ ነበር ማለት ነው (አላህ ይጠብቀንና) የሚያሳዝነው ይህንን ገለፃ ጳውሎስ ሳይደብቅ ያስቀምጠዋል

*" በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን፤"*

*(ገላ 3: 13)*

**ኢየሱስን ተሰቅሏል ብሎ ማመን እርሱን መርገምን ይጨምራል ማለት ነው። እንዴት ሰው አምላክ ብሎ የሚያስበውን አካል እየረገመ ያመልከዋል?**

ጠያቂው ልብ ባይለው እንጂ ለዚህ ጥያቄ ሐዋርያው ጳውሎስ መልስ ሰጥቷል፡-

> *በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን፡፡” (ገላቲያ 3፡13)፡፡*

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ከእርግማን ነፃ ሊያወጣን ሲል የእግዚአብሔርን ሕግ በመተላለፋችን ምክንያት የመጣብንን እርግማን ተሸከመልን፡፡ የተረገሙት የእግዚአብሔርን ሕግ የተላለፉት የሰው ልጆች እንጂ ክርስቶስ አይደለም፡፡ እርሱ የኛን ቅጣት ተሸክሞ ከእርግማን ነፃ ያወጣን ቤዛችን ነው፡፡

**35. ለምን ተጠራጠሩ?**

**ደቀመዛሙርቱ እየሱስን በገሊላ ባገኙት ወቅት ተጠራጥረው ነበር። (ማቴዎስ 28:17) ለምን ተጠራጠሩ? ምን አይነት ጥርጣሬስ ነበር በውስጣቸው የነበረው? እየሱስ ከነአካቴው አለመሠቀሉንና በአምላክ መዳኑን ነበር የሚያስቡት? ወይንስ ከፊታቸው የቆመው እሱ መሆኑን አላመኑም ነበር?**

ደቀ መዛሙርቱ እንደ እኛው ሰዎች በመሆናቸው በተለያዩ ምክንያቶች ለጥርጣሬ ሊዳረጉ ይችላሉ፡፡ ሆኖም ስቅለቱ በአደባባይ የተፈፀመ ስለነበር ከቶ ሊጠራጠሩ አይችሉም፡፡ ጥርጣሬ የተባለውም ሁኔታው ሁሉ ከአእምሮ በላይ ሆኖባቸው ግራ የመጋባት ስሜት ወይንም ኢየሱስን በማየታቸው ምክንያት ደስታቸው እጅግ አይሎ የስስት ዓይነት ስሜት ውስጥ ገብተው ሊሆን ይችላል (ሎተሪ የደረሰው ሰው ‹ዓይኔ ነው ወይስ እውነት ነው?› እንደሚለው ዓይነት)፡፡ አናውቅም፡፡ ዳሩ ግን ምንም ያህል አሳማኝ ማስረጃ ቢኖር ጥርጣሬ የሰው ልጆች ባሕርይ በመሆኑ ሊያስደንቀን አይገባም፡፡ ቁርአንስ ቢሆን መሐመድ ተጠራጣሪ እንዳይሆን በተደጋጋሚ ያስጠነቅቀው የለምን?

**36. መልካም ዛፍ**

ኢየሱስ ሲናገር እንዲህ ይላል፡-

*"እንዲሁ መልካም ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬ ያደርጋል፥ ክፉም ዛፍ ክፉ ፍሬ ያደርጋል። መልካም ዛፍ ክፉ ፍሬ ማፍራት፥ ወይም ክፉ ዛፍ መልካም ፍሬ ማፍራት አይቻለውም።" (ማቴ 7:17-18)*

በዚህ አንቀፅ እየሱስ እንደሚነግረን መልካም ፍሬ ማፍራት የሚችለው መልካም ዛፍ ነው። በሌላ አነጋገር ውጤቱ መልካም የሚሆነው መሠረቱ መልካም የሆነ ነገር ነው። መሠረቱ የተበላሸ ነገር መልካም ፍሬን ሊሰጥ አይችልም።

በዚህ አስተምህሮ መሠረት የኢየሱስን ስቅለት ስንፈትሸው ፍፁም ከአስተምህሮው ያፈነገጠ ሁኖ እናገኘዋለን። የኢየሱስ ግርፋት፣ስቃይና መገደል መሠረታቸው መጥፎ የሆኑ ተግባራት ናቸው። ታዲያ እነዚህ አስከፊ የወንጀል ተግባራት እንዴት ለአለም የሚሆን ማዳንን ማምጣት ይችላሉ? መልካም ዛፍ እንጅ መጥፎ ዛፍ እንዴት መልካም ፍሬ ሊያፈራ ይችላል?

አንደኛ፡- ኢየሱስ ስለ መልካምና ክፉ ዛፍ የተናገረው የነቢያትን አስተምሕሮ በተመለከተ ነው፡፡ የእውነተኛ ነቢያት ትምሕርት መልካም ፍሬ እንደሚያፈራና የሐሰተኛ ነቢያት ትምሕርት ደግሞ ክፉ ፍሬ እንደሚያፈራ እያስረዳ ነው (መሐመድ ሐሰተኛ ነቢይ በመሆኑ ምክንያት የትምሕርቱ ፍሬ ሽብርና እልቂት እንደሆነው ማለት ነው)፡፡

ሁለተኛ፡- ይሁን እንኳ ብንል ጠያቂው ዛፍን በፍሬው ሳይሆን ፍሬውን በዛፍ በመመዘን በዚህ ቦታ ከተቀመጠው መርህ አፈንግጧል፡፡ መጀመርያ ዛፉ (በኢየሱስ ላይ የደረሰው መከራና ሞት) ክፉ እንደሆነ ከደመደመ በኋላ ውጤቱም መልካም ሊሆን እንማይችል ይነግረናል፡፡ የቃሉ መርህ ግን አንድን ትምሕርት በውጤቱ እንድንገመግም እንጂ ውጤቱን በትምሕርቱ እንድንገመግም የሚል አይደለም፡፡ ስለዚህ የቃሉን መርህ ከተከተልን የኢየሱስ ሥቃይና ሞት ውጤቱ ሰላም፣ በረከትና ለሰው ልጆች ደህንነት በመሆኑ በመጥፎነት ላይፈረጅ ነው፡፡ ይህ ከመርሁ አኳያ ስሙር አመክንዮ ነው፡፡

ሦስተኛ፡- መሥዋዕት ሥቃይና መከራ አለበት፤ ነገር ግን ውጤቱ መልካም በመሆኑ መልካም እንጂ ክፉ ሊባል አይችልም፡፡ ለምሳሌ ያህል በክርስትናም ሆነ በእስልምና መከራ ደርሶባቸው ሰማዕታት የሆኑ አማኞች ሽልማት ያገኛሉ፡፡ ሽልማቱ መልካም ነገር ነው፡፡ ነገር ግን ሽልማቱ የሥቃይና የሞት ውጤት ነው፡፡ ስለዚህ ሥቃይና ሞት መጥፎ ናቸውና ከፈጣሪ ዘንድ በውጤታቸው የተገኘው ሽልማት ክፉ ነው ልን ነው? በፍፁም! ማን ያውቃል የላቀውን ሽልማት ከእግዚአብሔር ዘንድ የተቀበሉት ወገኖች ምናልባት ለዚያ ያበቃቸውን ሥቃይና ሞት እንደ መልካም አጋጣሚ በመቁጠር ያመሰግኑት ይሆናል፡፡ እኛ እንደ ክፉት የቆጠርነው አጋጣሚ በዚያኛው ዓለም ውስጥ ሆነው የተሻለ የዕይታ ፅንፍ ባገኙት ቅዱሳን ዘንድ መልካም ገፅታው ይታያል ማለት ነው፡፡


37. <u>እሱን ማሰር ትልቅ ሀጥያት ነው</u>

*" ኢየሱስም መልሶ፡- ከላይ ካልተሰጠህ በቀር በእኔ ላይ ምንም ሥልጣን ባልነበረህም፤ ስለዚህ ለአንተ አሳልፎ የሰጠኝ ኃጢአቱ የባሰ ነው አለው።"*

*(ዮሐ 19: 11)*

እየሱስን እንዲሰቀል አሳልፎ መስጠት ትልቅ ሀጥያት እንደሆነ ኢየሱስ ይናገራል። ታዲያ ሀጥያት የሆነ ተግባር እንዴት የመዳን መሠረት ሊሆን ይችላል? ክርስቲያኖች በስቅለት ድነናል ሲሉ ተግባሩ ሀጥያት ነውና በሀጥያት ድነናል እያሉ መሆኑን አስተውለዋል?

ይህንን ጥያቄ በቁጥር 32 እና በቁጥር 36 ላይ መልሰናል፡፡ አይሁድና ጲላጦስ በኢየሱስ ሞት ምክንያት ተጠያቂ የሚሆኑት በልብ ሐሳባቸው (intention) ምክንያት ነው፡፡ ተግባራቸው ንፁሁን ሰው በማጥፋት አጀንዳቸውን ከግብ ማድረስ በመሆኑ ተጠያቂዎች ናቸው፡፡ የኢየሱስ ሞት ለገዳዮቹ በክህደታቸው ምክንያት ኃጢአት ሲሆን ለአማኞቹ ደግሞ በእምነታቸው ምክንያት ጽድቅ ነው፡፡ ልክ አንድ ሰማዕት ገዳዮቹ ኃጢአትን በመሥራታቸው ምክንያት የእርሱ ሞት ለእርሱም ሆነ ለሌሎች መልካም ውጤትን ማስገኘቱ እንደማይቀር ሁሉ የኢየሱስ መሥዋዕትነትም ገዳዮቹ ኃጢአትን በመሥራታቸው ምክንያት ለሰው ልጆች የመዳን ምክንያት መሆኑ አይቀርም፡፡



### 38. ኢየሱስ ይሁዳን ረግሞታል

ኢየሱስ ሲናገር እንዲህ ይላል፡-

*" የሰው ልጅስ ስለ እርሱ እንደ ተጻፈ ይሄዳል፥ ነገር ግን የሰው ልጅ አልፎ ለሚሰጥበት ለዚያ ሰው ወዮለት፤ ...*

*(ማቴ 26: 24)*

ነገር ግን የስቅለቱን ጉዳይ እውን ማድረግ የቻለው ይሁዳ ነበር። ይሁዳ ባይኖር ኑሮ ስቅለቱም ባልተካሄደ ክርስቲያኖችም "ባልዳኑ" ነበር።እዛው አንቀፅ ታች ላይ ወረድ ብሎ ኢየሱስ እንዲህ ይላል፡-

*"...የ ሰው ባልተወለደ ይሻለው ነበር አለ።" ማቴ 26:24*

ይሁዳ ባይወለድ ኖሮ የስቅለቱ ታሪክ እንዴት ይኖር ነበር? ስቅለት ከሌለ ደግሞ ትንሳኤ የለም። ትንሳኤ የለም ማለት ደግሞ ከነአካቴው ክርስትና የለም ማለት እንደሆነ ጳውሎስ አስተምሯል።

*"ክርስቶስም ካልተነሣ እንግዲያስ ስብከታችን ከንቱ ነው እምነታችሁም ደግሞ ከንቱ ናት፤" (1 ቆሮ 15: 14)*

ይህ ሁሉ የአስተምህሮ መፋለስ የመጣው ከመነሻው በተፈጠረ ስህተት እንደሆነ ተረዳችሁ? ከመነሻው አንድ ሰው ለመዳን ስቅለት ያስፈልጋል ብሎ ሲያምን እነዚህን ሁሉ ዝብርቅርቅ ፅንሰሀሳቦች ከነወረደ በጭፍን እያመነ ነው ማለት ነው።

*"... አልገደሉትም አልሰቀለቱምም ..." ቁርአን 4:157*

የአንድ ሰው ምግባር ጥሩነት የሚለካው በውጤቱ ብቻ ሳይኾን በፍላጎትና በዓላማውም ጭምር ነው፡፡ ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ ሲሰጠው በኢየሱስ ላይ ክህደትን በመፈፀም ገንዘብ ለማትረፍ እንጂ የኢየሱስን ተልዕኮ ከግብ በማድረስ ዓለምን ለማዳን አልነበረም፡፡ ይሁዳ ለክፋት ያሰበውን እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ዕቅዱን ለማስፈፀም መጠቀሙ ይሁዳን ከወንጀሉ ነፃ አያደርገውም፡፡ የጠያቂው አመክንዮ ትክክል ከሆነ በየዘመናቱ የእግዚአብሔርን አገልጋዮች በመግደልና በማስገደል ለተሻለው የሰማዕትነት ክብር እንዲበቁ ምክንያት የሆኑ ክፉ ሰዎች ኹሉ ሊሸለሙ ይገባል ማለት ነው፡፡ ለምን ቢሉ እነዚያ ሰዎች ባይገድሏቸውና ባያስገድሏቸው ኖሮ ለሰማዕትነት ክብር በመብቃት የተሻለውን ሽልማት ባልተቀበሉ ነበር፡፡ ይህ ሙግት መሠረታዊ የማመዛዘን ችሎታ ካለው ሰው አይጠበቅም፡፡ የወደቀ ሙግት ነው፡፡ ገለባ ነው! (ለአሕመዲን ጀበል ከተሰጠው መልስ የተወሰደ)፡፡

የቁርአኑ ጥቅስ "አልገደሉትም አልሰቀሉትምም" ይላል እንጂ "አልተገደለም አልተሰቀለም" አይልም፡፡ ለዚህ ነው የአሕመዲያና የኔሽን ኦፍ ኢስላም ሙስሊሞች ዒሳ በሮማውያን እንደተገደለና በአይሁድ እንዳልተገደለ የሚያምኑት፡፡ "አልገደሉትም አልሰቀሉትምም" ማለት አይሁድ "አልገደሉትም አልሰቀሉትም" ማለት እንጂ ሮማውያን "አልገደሉትም አልሰቀሉትም" ማለት አይደለም ይላሉ፡፡ እንዲህ ዓይነቱን አሻሚ ትርጉም ያለውንና ሙስሊሞችን ሳይቀር ለክፍፍል የዳረገውን ጥቅስ ነው እንግዲህ ጠያቂው እንደ "ማስረጃ" የሚጠቅሱልን፡፡ ይገርማል!

### 39. <u>አምላክን መግደል</u>

አምላክ ሁላችንም እንደምናውቀው ሁሉን ቻይና ሀያል ነው። ይህን ሁሉ ቻይና ሀያል የሆነ አምላክ ከዛሬ ሁለት ሺህ አመት በፊት ሰዎች ገድለውታል ብሎ ማመን በራሱ ፌዝ ነው። በአምላክ ክብር ላይ ማላገጥም ጭምር ነው። አምላክ በምንም መስፈርት ቢሆን ከሙታንነት ባህሪ የጠራ ነው። እንደፍጡራኖቹ ስቃይንና ሞትን ይጋፈጣል ብሎ ማመንና መስበክ አንድም ስለአምላክ ያለን አመለካከት መዛባት ሁለትም ክህደት ነው። ኢየሱስ ሶስት ቀንና ሶስት ሌሊት ሙቷል ተብሎ የሚታመን ከሆነ የአምላክ ባህሪ ውስጥ አንዱ የሆነው ዝንታለማዊነት ኢየሱስ አያሟላም ማለት ነው። ያ ማለት ደግሞ ኢየሱስ ከስላሴዎች ጋር እኩሎ የሆነ ስልጣን የለውም ማለት ነው።

ይህንን ጥያቄ ማንኛም መጽሐፍ ቅዱስን ያነበበ ሰው ሊመልሰው ይችላል፤ የጠለቀ ዕውቀት አይጠይቅም፡፡ መልሱ ሁለት ዓይነት ነው፤ መጀመርያ ሞት ማለት አለመኖር ማለት አይደለም፡፡ እግዚአብሔር መኖር አቆመ እያልን አይደለም፡፡ ሁለተኛ አምላክ ሊሞት አለመቻሉ እውነት ቢሆንም ኢየሱስ በአንድ ማንነት ሁለት ባሕርያት (መለኮታዊና ሰብዓዊ ባሕርያት) አሉት፡፡ በሰብዓዊ ባሕርዩ ነው የሞተው፡፡ ይህ አምላክ ኢ-ሟቲ ከመሆኑ እውነታ ጋር አይጣረስም፡፡

### 40. <u>አስተምህሮውና እየሱስ</u>

እየሱስ የአዳም ሀጥያትን አስመልክቶ እንዲሁም በዛ ምክንያት ለሰው ልጆች ሀጥያት ስርየት ሊፈጽም እንደመጣ ግልፅ ባለ ሁኔታ አልተናገረም። ይህ የክርስትና መሠረታዊ ክፍል በእየሱስ ከምንም በላይ በሰፊው ሊብራራ ሲገባው ከመነሻው እንኳን አለመጠቀሱ አስተምህሮው ከእየሱስ በኃላ የተፈበረከ ዶግማ እንደሆነ ማሳያ ነው።

አዳም ኃጢአት መሥራቱና በኃጢአቱ ውጤት ምክንያት የሰው ልጆች ከገነት መባረራቸው ገና በመጀመርያው የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ የመጀመርያዎቹ ምዕራፎች ውስጥ ተጠቅሶ ሳለ፤ ነቢያትም መሲሁ በመምጣት ለሰው ልጆችን ኃጢአት እንደሚሞት ተናግረው ሳሉ ትምሕርቱ ከኢየሱስ በኋላ ነው የመጣው እንዴት ይባላል (ዘፍጥረት 3፣ ኢሳይያስ 53)? ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስ ወደ ሐዋርያቱ በመምጣት ብዙ ትምሕርቶችን እንደሚያስተምራቸው ተናግሮ ሳለ የኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ ዓላማ በሐዋርያት መብራራቱ ጥያቄን የሚፈጥረው እንዴት ሆኖ ነው?

> *“አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኳችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል።” (ዮሐንስ 14፡26)፡፡*

41. መዳን በትዕዛዝ ነው

ከላይ እንዳየነው እየሱስ ስቅለቱ የሰው ልጅ የመዳኛ መንገድ እንደሆነ አልጠቀሰም ነበር። ስለመዳን ለጠየቁት ሰዎችም የመለሳላቸው መልስ አይደለም ስቅለቱን አስመልክቶ ሊሆን ይቅርና መዳንን ከሱ ጋር ሲያይዘው ፈጽሞ አናስተውልም። በማቴወስ ወንጌል እንደተጠቀሰው እየሱስ መዳን የሚገኘው ትዕዛዛትን በመጠበቅ እንደሆነ ገልጿል።

*"እነሆም፥ አንድ ሰው ቀርቦ፡- መምህር ሆይ፥ የዘላለምን ሕይወት እንዳገኝ ምን መልካም ነገር ላድርግ? አለው። እርሱም፡- ስለ መልካም ነገር ለምን ትጠይቀኛለህ? መልካም የሆነ አንድ ነው፤ ወደ ሕይወት መግባት ብትወድ ግን ትእዛዛትን ጠብቅ አለው።"*

ማቴ 19፥16-17

ኢየሱስ ስቅለቱ የሰው ልጆች መዳኛ መሆኑን በተደጋጋሚ ጠቅሷል፡-

> *“ሙሴም በምድረ በዳ እባብን እንደ ሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ይገባዋል። በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።” (ዮሐንስ 3፡14-16)*

> *“ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ ባረከ ቈርሶም ሰጣቸውና፡- እንካችሁ፤ ይህ ሥጋዬ ነው አለ። ጽዋንም አንሥቶ አመስግኖም ሰጣቸው፥ ሁሉም ከእርሱ ጠጡ። እርሱም፡- ይህ ስለ ብዙዎች የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ነው።” (ማርቆስ 14፡22-24)*

መዳን ትዕዛዛትን በመጠበቅ ይገኛል፡፡ ነገር ግን ሁሉንም ትዕዛዝ በትክክል መጠበቅና በአንዱም አለመሳሳት ያስፈልጋል፡፡ አንዱን ትዕዛዝ የተላለፈ ሰው ሁሉንም እንደተላለፈ ይቆጠራል (ያዕቆብ 2፡10)፡፡ ነገር ግን ችግሩ እንዲህ ዓይነት ሰው በሰው ልጆች ታሪክ ያልነበረና ሊኖርም የማይችል መሆኑ ነው፡፡ ለዚህ ነው አምላክ የሆነው ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ወደ ምድር የመጣው፡፡ በእስልምናም ሆነ በክርስትና ፍፁም ኃጢአት የሌለበት ብቸኛው ንፁህና ጻድቅ ሰው እርሱ ነው፡፡ እርሱ የኃጢአት ዕዳችንን ተሸከመልን፡፡ ለሰው የማይቻለው በእርሱ ተቻለ፡፡

ጠያቂው በጠቀሰው ጥቅስ ውስጥ ባለጠጋው ወጣት ሕግን ሁሉ እንደፈፀመ በኩራት ሲናገር ኢየሱስ ግን ሕግን ሁሉ አለመፈፀሙን ሊያስገነዝበው ያለውን ሁሉ ሸጦ ለድሆች በማካፈል በፍፁም ልቡ እንዲከተለው ነገረው፡፡ ሆኖም ያንን ትዕዛዝ መፈፀም አልቻለም፡፡ በማስከተል እንዲህ ይላል፡-

> *“ዳግመኛም እላችኋለሁ፥ ባለጠጋ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢገባ ይቀላል አለ። ደቀ መዛሙርቱም ሰምተው እጅግ ተገረሙና፡- እንኪያስ ማን ሊድን ይችላል? አሉ። ኢየሱስም እነርሱን ተመልክቶ፡- ይህ በሰው ዘንድ አይቻልም በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ሁሉ ይቻላል አላቸው።” (ማቴዎስ 19፡24-26)*

ደህንነትን በሥራ ማግኘት በሰው ዘንድ አይቻልም፡፡ ነገር ግን በእግዚአብሔር ዘንድ ይቻላል፡፡ እኛ ያልቻልነውን ክርስቶስ ችሎልናል፡፡

42. መዳን በስቅለት ነው?

የክርስቲያኖች መዳን የተመሠረተው በስቅለት ላይ ነው የሚባል ከሆነ የዚህ መዳን ትልቅ ተመስጋኞች አይሁዳውያን፣ ሮማውያንና ይሁዳ ናቸው ማለት ነው። ምክንያቱም

1- ይሁዳ አሳልፎ ባይሰጠው ስቅለቱ ተግባራዊ አይሆንም ነበር

2- አይሁዳውያንም ለጲላጦስ እንዲሰቅለው ባያደርጉት ኖሮ አሁንም ስቅለቱ ተግባራዊ አይሆንም ነበር

3- በመጨረሻም ሮማውያን ውሳኔውን አስፈጽመው ባይሰቅሉት ኖሮም መዳኑ አይመጣም ነበር።

ይህ ማለት ለክርስቲያኖች እምነት እነዚህ ሶስቱ ከፍተኛ ቦታ አላቸው ማለት ነው። እንደጠላት ሳይሆን እንደ ወዳጅ ሊታዩ የሚገባ አካላት ናቸው። ነገር ግን ስቅለት መሠረቱ ልክ ካለመሆኑ አንፃር እነዚህን በተቃራኒ ጠላት አድርጓቸዋል።

ይህንን ጥያቄ በቁጥር 38 ላይ መልሰናል፡፡ የአንድ ሰው ምግባር ጥሩነት የሚለካው በውጤቱ ብቻ ሳይሆን በፍላጎትና ዓላማውም ጭምር ነው፡፡ ይሁዳ በገንዘብ ወዳድነት፣ አይሁድ በቅንዓት፣ ሮማውያን ደግሞ ለሥልጣናቸው ሲሉ የፈፀሙትን ተግባር እግዚአብሔር በሉኣላዊ ሥልጣኑ ለበጎ መጠቀሙ እነዚህን ወገኖች ከወንጀሉ ነፃ አያወጣቸውም፤ ወዳጅም እንዲሆኑ አያደርጋቸውም፡፡ የጠያቂው አመክንዮ በጣም ደካማ ነው፡፡

--//--

**ያህያ ሆይ እንዲህ ዓይነት ገለባ የኩረጃ መጽሐፍ ለማሳተም ነው አረብ አገር ከሚሠቃዩት እህቶቻችን ገንዘብ የሰበሰብከው? ኢየሱስ ክርስቶስ መንገድም፣ እውነትም ሕይወትም ነው! እስልምና ሐሰትና የሞት መንገድ ነው! በሐሰት ለሐሰት ከምትሟገት ወደ ክርስቶስ ብርሃን ናና ነፃ ውጣ! በእንቢታህ ከፀናህ ግን ለስህተትህ ብቻ ሳይሆን ለምታሳስታቸውም ወገኖች ሕይወት ጭምር በእግዚአብሔር ፊት መልስ ትሰጣለህ!**